**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፡፡**

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ትምህርት ሣልሳይ፡- ምዕራፍ ሦስት

# ክፍል አንድ፡- ብሉይ ኪዳን

ጥያቄ፡- አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ምን ተብለው ይጠራሉ?

መልስ፡- አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት በአራማይክ «ኦሪት» ይባላሉ ብርሃን ማለት ነው፡፡ በዕብራይስጥ «ቶራ» ነው፡፡ መመሪያ ማለት ነው፡፡ በፅርዕ ደግሞ «ኖሞስ» ይባላሉ፡፡ «ሕግ» ማለት ነው፡፡

ጥያቄ፡- አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ስለምን ያስተምራሉ?

መልስ፡- **«ኦሪት ዘፍጥረት»** የሰውን ልጅ ተፈጥሮና ድምሳሴ ያሳያል፡፡ 50 ምዕራፍ አለው፡፡

**«ኦሪት ዘፀአት»** የሰውን ዘር ከጥፋት መመለስና መዳን ያሳያል፡፡ 40 ምዕራፍ አለው፡፡

**«ኦሪት ዘሌዋውያን»** መሥዋዕትንና አምልኮትን ያስተምራል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አምስት የመባ አይነቶች ተመዝግበዋል፡፡

ሀ. የሚቃጠል ለ. የምግብ ሐ. የሰላም መ. የኃጢአትና ሠ. የዱቄት፡፡ ይህ መጽሐፍ 27 ምዕራፍ አለው፡፡

**«ኦሪት ዘኁልቊ»** ይህ መጽሐፍ ቆጠራን ጉዞንና ጦርነትን ያሳያል፡፡ በምሥጢረ ሥጋዌም ጌታ የተሰየመባቸውን አራት ስሞች ይዟል፡፡

ሀ. የሕይወት እንጀራ ምዕ 11፣7-9 ለ. የሕይወት ውሃ ምዕ 20፣11 ሐ. አርዌ ብርት ምዕ 21፣9 መ. የያዕቆብ ኮከብ ምዕ. 24፣17

ይህ መጽሐፍ 36 ምዕራፍ አለው፡፡

**«ኦሪት ዘዳግም»** ይህ መጽሐፍ ሙሴ ባራቱ መጻሕፍት የተናገራቸውን እንደገና የሚያስታውስ ነው፡፡ ሦስት ክፍል አለው፡፡

ሀ. በምድረ በረዳ እግዚአብሔርን ማምለክ ምዕራፍ 1 - 11

ለ. ሕግና ምድረ ርስት ምዕራፍ 12 - 19

ሐ. ጸጋና መንግሥት ምዕ 30 - 31፡፡ ኦሪት ዘዳግም 34 ምዕራፍ አለው፡፡

**«መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ»፡-** በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በኢያሱ መሪነት እስራኤል ወደ ምድረ ርስት ወደ ኢየሩሳሌም መግባታቸው ተተርኳል፡፡ ይህም በክርስቶስ መስቀል መሪነት ክርስቲያኖች ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ወደ መንግሥተ ሰማያት የመግባታቸው ምሣሌ ነው፡፡ ኢያሱ መማጠኛ እንዲሆኑ የከለላቸው ስድስት ቦታዎች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተገልጠዋል፡፡ እነርሱም፡-

ሀ. ቃዴስ ለ. ሴኬም ሐ. ኬብሮን /ቂርያት አርባቅ/ መ. ቦሶር ሠ. ራሞት ረ. ጎላን /ኢያሱ 20÷7- 9/ ናቸው፡፡

ይህ መጽሐፍ 24 ምዕራፍ አለው፡፡

**«መጽሐፈ መሳፍንት»፡-** «ዳኞች» «ጠበቆች»/ ዳኛ ማለት በዕብራይስጡ ልማድ የተሳሳተውን ነገር የሚያስተካክል ነው፡፡ ከኢያሱ ወልደ ነዌ በኋላ እሥራኤልን 13 ዳኞች/መሳፍንት / አስተዳድረዋቸዋል፡፡ ከነዚህም አሥራ ኹለቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተመረጡ ሲኾኑ አቤሜሌክ ግን በጉልበቱ የተነሳ ነበር፡፡ /መሳፍንት 9÷ 22፣23፡፡/ አሥራ ሦስቱ ዳኞች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ጎቶንያል
2. ናኦድ/ግራኙ/
3. ሳሚጋር
4. ዲቦራና ባርቅ
5. ጌዲዎን
6. አቤሜሌክ
7. ቶላ
8. ኢያዕር
9. ዮፍታሔ
10. ኢብዳን
11. ኤሎም
12. አብዶን
13. ሶምሶን/ሳምሶን/ ናቸው

እነዚህ አሥራ ሦስቱ ዳኞች እስራኤልን ለ300 ዓመታት አስተዳድረዋል:: ይኸውም ሳኦል እስኪነግስ ድረስ ማለት ነው:: መጽሐፈ መሳፍንት 21 ምዕራፍ አለው:: በዚህ አኳኋን የእስራኤል መሪዎች አራት ክፍል ነበሩ:: እነሱም:- ሀ. ካህናት ለ. ዳኞች ሐ. ነቢያት መ. ነገሥታት::

«መጽሐፈ ሩት»:-

ሩት አረማዊት ናት እስራኤላዊው ቦኤዝን አግብታ ትኖር ነበር:: ከሱም ኢዮቤድን ወለደች የእግዚአብሔር ምርጫ እስራኤልን ብቻ ሳይኾን አሕዛብንም ኹሉ መኾኑን ከዚች ሴት እንማራለን:: መጽሐፈ ሩት አራት ምዕራፍ አለው:: አምስቱ የሙሴ መጽሐፍት፣ ኢያሱና መሳፍንትን ሩትንም ጨምሮ ስምንቱ ብሔረ ኦሪት ይባላል:: የኦሪት ክፍል የኦሪት ዘርፍ ማለት ነው::

«መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ»:-

ስለ ሳሙኤል ልደትና ዕድገት፣ ሥለ አመራር ስለ መጀመሪያ የእስራኤል ንጉሥ ሳኦል አነሳስ፣ስለ ዳዊት መነሳት፣ ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤል ጋር ስላደረጉት ጦርነት፣ ስለ ታቦተ ጽዮን መማረክ ይተርካል:: መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 31 ምዕራፍ አለው::

«መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ»:-

ስለ ዳዊት መንገሥ፣ ስለ ታቦተ ጽዮን መመለስ ይተርካል:: መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 24 ምዕራፍ አለው::

«መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ»:-

ስለ ዳዊት መሞት፣ ስለ ሰሎሞን መንገሥ፣ ሰባት ዓመት ስለፈጀው የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ ሥራ፣ ስለ ንግስት ሣባ ጉብኝት፣ስለ ሰሎሞን መሞት፣ ስለ ሮብአም መንገሥና የእስራኤል ለኹለት መከፈል፣ የነቢየ እግዚአብሔር ኤልያስና የእስራኤል ቤተ መንግሥት ጠብ በደሀው በናቡቴ ምክንያት እየተካረረ መሔዱ በዚህ መጽሐፍ ተተርኳል:: መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 22 ምዕራፍ አለው::

«መጽሐፈ ነገስት ካልዕ»:-

የእስራኤል መንግሥት ለኹለት ከተከፈለ በኋላ ሰሜኑ ክፍል በአሶራውያን፣ ደቡቡ ክፍል ደግሞ በናቡከደነፆር መወረሩን ይተርካል:: መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 25 ምዕራፍ አለው::/በኹለቱም መጽሐፈ ነገሥት የተተረከው የ400 ዓመት ታሪክ ነው::/

«መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ»:- ስለ እስኤል ሐረገ ትውልድ ዝርዝር ጥናትና በተለይም ስለ ዳዊት የሕይወት ታሪክ አብራርቶ ይተርካል:: ይህ መጽሐፍ 29 ምዕራፍ አለው::

«መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ»:- አዲሱና የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ በዐውደ ኦርና ተሰርቶ መፈጸሙንና መባረኩን የይሁዳ ነገሥታት በስሜታቸው ተገፍተው ልዩ ልዩ ጣኦታትን ማቆማቸውን፣ በመጨረሻም የኢየሩሳሌም ጥፋት ይተርካል::/በመጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ የዳዊት መመረጥ ዋናው ርዕስ ነው፣ ነገሥት ቀዳማዊ የእስራኤልን መንግሥት አፍአዊ ታሪክ ይተርካል:: ኹለቱ ዜና መዋዕል ደግሞ ስለ ሰሎሞን፣ ኤልያስና ኤልሳዕ ጀምረው ይናገራሉ::/ ዜና መዋዕል ካልዕ 36 ምዕራፍ አለው::

«የዕዝራ መጽሐፍ»:- ከሰባ የምርኮ ዓመት በኋላ እስራኤል ከባቢሎን መመለሳቸውን፣ የቂሮስ አዋጅ፣ የእስራኤል መመለስ፣ ቤተ መቅደስ እንደገና እንዲሰራ ዳርዮስ ያስተላለፈውን አዋጅ ይተርካል:: 10 ምዕራፍም አለው::

« የነህምያ መጽሐፍ»:- ስለ ቤተ መቅደስ መሠራት /ቤተ መቅደስ በ537 ተጀምሮ በ515 ከጌታ ልደት በፊት ተፈጸመ::/ ስለ ኢየሩሳሌም ቅጥር መታደስ /ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጽር አስገንብቶ ያበቃው በ444 B.C. ከጌታ ልደት በፊት ነው::/ ኢየሩሳሌም አሥራ ሁለት በሮች እንደነበሯት ነህምያ ተናግሯል:: ነህምያ ማለት «ከአምላክ የተሰጠ አጽናኝ» ማለት ነው:: አስራ ሶስት ምዕራፍ አለው::

«መጽሐፈ አስቴር»:- በመፍሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በሴት ስም የተጠሩ ሦስት መጽሐፎች አሉ:: እነሱም:- ሩት፣ ዮዲት፣ አስቴር ናቸው:: የአስቴር መጽሐፍ የእስራኤልን ዝርወት፣ የእግዚአብሔርን አዳኝነት ይተርካል:: አሥር ምዕራፍ አለው::

«መጽሐፈ ኢዮብ»:- ክፋት በተሞላበት ዓለም ጻድቃን እንዴት ባለ ስቃይ እንደሚኖሩ፣ ኢዮብና ሰይጣን፣ ፍትሐ እግዚአብሔር፣ ኢዮብና ሦስት ጓደኞቹ ያደረጉት ውይይት/ኤልፋዝ፣ ባልዳዶስ፣ ሶፋር/ የኢዮብ ስቃይ የሚስቱ ክፉ ምክር፣ የኢዮብ ትዕግስት፣ እግዚአብሔርና ኢዮብ በጨረሻም የኢዮብ መንፈሳዊና ስጋዊ ሀብቱ እንደተመለሰለት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሰፍሯል:: ይህም አርባ ሁለት ምዕራፍ አለው::

<u>«የዳዊት መዝሙር»:-</u> ይህ መጽሐፍ 150 መዝሙሮች አሉት፡፡ እነዚህ መዝሙሮች ትንቢትን ምክርን፣ ውዳሴን፣ ምስጋናን ያጠቃለሉ ናቸው፡፡

<u>«መጽሐፈ ምሳሌ»:-</u> ሰሎሞን ሦስት ሺ ምሳሌዎችን ተናግሯል /ቀዳ. ነገሥት.4÷ 29-35/ በዚህ መጽሐፈ ምሳሌ 13 ምክርና ጥበብ አዘል ምሳሌዎች አሉ፡፡ መጽሐፈ ምሳሌ 31 ምዕራፎች አሉት፡፡

<u>«መጽሐፈ መክብብ»:-</u> ይህም የሰሎሞን መጽሐፍ ነው፡፡ ስለ አለም ከንቱነት ስለ ጥበብ ልዕልና ስለ እግዚአብሔር ኀቡዕ ምስጢር ይናገራል፡፡ መጽሐፈ መክብብ አስራ ሁለት ምዕራፍ አለው፡፡

<u>«መኃልየ ሰሎሞን»:-</u> ሰሎሞን 1005 መኃልይ ተናግሯል /ቀዳ. ነገሥት. 4÷29-35/ ይህ የመኃልይ ክፍል ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የእግዚአብሔርና የምዕመናን መፈላለግ፣ ምሳሌ የኾነችው የሱላማጢስና  የሰሎሞን መፈላለግ፣ የሰሎሞን ቤተ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን፣ የሰሎሞንና የሱላማጢስ ፍቅር የክርስቶስንና የምእመናንን ፍቅር የሚያሳይ ሥዕል ኹኖ ቀርቧል፡፡ መኃልይ ስምንት ምዕራፍ አለው፡፡

<u>«ትንቢተ ኢሳይይስ»:-</u> «ኤልያሁ» «የእግዚአብሔር ደኅንነት ነው» ማለት ነው፡፡ ትንቢቱን የጀመረው በአስራ አምስት ዓመት ዕድሜው ነው፡፡ ይኸውም እንደ ሳሙኤል፣ እንደ ኤርምያስና ዳንኤል ነው፡፡ በተወለደ በ85 ዓመቱ ምናሴ በመጋዝ አሰንጥቆ ገድሎታል፡፡ ኢሳይያስ በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን/ከጌታ ልደት በፊት / ነበረ፡፡ የኢሳይያስ መጽሐፍ 66 ምዕራፍ አለው፡፡ በውስጡም ካሉት ነጥቦች:-

ሀ. በዘመኑ የነበረው አስቸጋሪ ሁኔታ፣

ለ. የራሱ ጥሪ ለነቢይነት

ሐ. ድንግልና አማኑኤል

መ. የጽዮን ክብርና ውርደት

ሠ. የመሢህ ሕማማተ መስቀል ዋናዎቹ ናቸው፡፡

<u>«ትንቢተ ኤርምያስ»:-</u> «ኤርምያኹ» ማለት #እግዚአብሔር ከፍ ያደርጋል; ማለት ነው፡፡ ዮሐንስ መጥምቅ በማሕጸን እንደሰገደ ኤርምያስ ገና በማሕጸን ሳለ የተጠራ ነቢይ ነው፡፡ ትንቢቱን የጀመረው በ627 ከጌታ ልደት በፊት ነው። በመጽሐፍ ከተጠቀሱት ዋና ነጥቦች:-

ሀ. የራሱ ጥሪ ለነቢይነት

ለ. ወደ ባሮክ የላከው መልዕክት

ሐ. አምስቱ ማስጠንቀቂያዎች /13 ፥ 1-27፡፡/ ይህ መጽሐፍ ሃምሳ ሁለት ምዕራፍ አለው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት በግብጽ እንዳለ አይሁድ በሰማዕትነት ገድለውታል፡፡

<u>«ሰቆቃወ ኤርምያስ»:-</u> ኤርምያስ የሰቆቃው ነቢይ ይባላል፡፡ የባቢሎናውያን ወረራ የኢየሩሳሌም ጥፋት፣ የቤተ መቅደስ መፍረስ ትዝ እያለው በሙሾ መልክ የጻፈው ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ዋናዎቹ:-

ሀ. የኢየሩሳሌም ባድማ መኾን

ለ. ኃጢአት የመከራ ግብዣ መኾኑ

ሐ. የርኅራኄ ጩኸት

መ. የረሀብ አስደንጋጭነት፣ የሐሰትና የእውነት ነቢያት

ሠ. የግፉአን ጩኸት፣ የእግዚአብሔር ምህረት፣የኃጢአት አሳፋሪነት

ረ. የእግዚአብሔር ዘላለማዊነት ናቸው፡፡ ይህ መጽሐፍ ሃያ ሁለት ክፍል አለው፡፡ ይኸውም በዕብራውያን ፊደል ልክ ነው፡፡ አምስት ምዕራፍ አለው፡፡

<u>«ትንቢተ ሕዝቅኤል»:-</u> ሕዝቅኤል ማለት «እግዚአብሔር ብርታትን ይሰጣል» ማለት ነው፡፡ ከኤርምያስ ጋር የነበረ ነው፣ ሃያ ሁለት ዓመት አስተምሯል፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ ዋናው ነጥብ:-

ሀ. ለነቢይነት መጠራቱ

ለ. የቤተ መቅደስ ሥዕል

ሐ. የድንግል ማርያም ምሳሌ የኾነችው የተዘጋች እልፍኝ፣ የእስራኤል እንደገና መቋቋም:: መጽሐፉ 48 ምዕራፍ አለው::

**<u>«ትንቢተ ዳንኤል»:-</u>** «ዳንኤል» ማለት «ዳኛዬ እግዚአብሔር ነው» ማለት ነው:: ዳንኤል በ615/ከጌታ ልደት በፊት / በኢየሩሳሌም ተወለደ:: የአሥር ዓመት ሕጻን ሳለ ወደ ባቢሎን ተማርኮ ተወሰደ፣ ለዳዊት ቤተ መንግሥት ልዑል ነበር:: በትንቢተ ዳንኤል ከተገለጠው በመጠኑ:-

ሀ. የዳንኤል ሥልጣን በባቢሎን

ለ. የናቡከደነጾርን ሕልም ዳንኤል ተርጉሞታል

ሐ. ሠለስቱ ደቂቅን ለማቃጠል የነደደው እሳት

መ. የዳንኤል ራዕይ ስለ ሐሳዊ መሲህ

ሠ. ስለ ጌታ ሕማማተ መስቀል:: /9፣25-26/ ዳንኤል በ534 /ከጌታ ልደት በፊት/ የሞተ ሲሆን ሲሞት 80 ዓመቱ ነበር:: የዳንኤል መጽሐፍ 12 ምዕራፍ አለው::/ከኢሳይያስ ጀምረን ያየናቸው አራቱ አበይት ነቢያት ይባላሉ:: ደቂቀ ነቢያት የሚባሉት በዘመን ሳይኾን በትንቢታቸው ማጠር ነው::/

**<u>«ትንቢተ ሆሴዕ»:-</u>** ሆሴዕ ማለት «ድህነት» ማለት ነው:: ከ60 ዓመት በላይ ትንቢት ተናግሯል:: ትንቢቱ በአሥሩ ነገድ በሰማርያ ነው:: መልዕክቱ ግን ይሁዳንም የሚመለከት ነው:: ሆሴዕ የነበረው ከ765 /ከጌታ ልደት በፊት/ ጀምሮ ነው:: ከትንቢተ ሆሴዕ ውስጥ:-

ሀ.የሆሴዕ ጥሪ

ለ. ስለ እግዚአብሔር ፍርድ፣ ንስሐና ዕርቅ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር ሕዝብና አሕዛብን እንደሚያገናኝ ተገልጧል:: ስለዚህ ሆሴዕ የብሉይ ኪዳን ዮሐንስ ይባላል:: የሆሴዕ መጽሐፍ አሥራ አራት ምዕራፍ አለው::

**<u>«ትንቢተ አሞጽ»</u>:-** አሞጽ ከበግ ጥበቃ የተጠራ ነቢይ ነው:: ይኸውም በ760 /ከጌታ ልደት በፊት/ ነው:: አሞጽ ማኅበራዊ ኑሮን ለማስተካከል የፍርድ ሚዛን እንዳያዳላ ትምህርት አሥተምሯል:: ስለዚህ የፍትህና የዳኝነት ነቢይ ይባላል:: በአሞጽ መጽሐፍ ውስጥ ከተነገሩት ዋናዎቹ:-

ሀ.የራሱ ከእረኝነት መጠራትና የእግዚአብሔር ፍርድ

ለ.እግዚአብሔርና ተስፋ፣ ትንቢትና ሃይማኖት ናቸው::

የአሞጽ መጽሐፍ ዘጠኝ ምዕራፍ አለው:: የአሞጽ የአገልግሎት ዘመን ከኹለት ዓመት አይበልጥም::

**<u>«ትንቢተ ሚክያስ»</u>:-** ሚክያስ ማለት «እንደ አምላክ ማነው» ማለት ነው:: በ751/ከጌታ ልደት በፊት / ለትንቢት ተጠራ:: በሚክያስ መጽሐፍ ከተጠቀሱት ዋና ዋና ነጥቦች:-

ሀ. የድሆች መበዝበዝ፣ ምስጋና ቢስ የሆኑትን ሰዎች እግዚአብሔር እንዴት እንደሚነቅፋቸው

ለ. የክርስቶስ ድል አድራጊነት በቤተ ክርስቲያን:: የሚክያስ መጽሐፍ ሰባት ምዕራፍ አለው::

**<u>«ትንቢተ ኢዮኤል»:-</u>** «ኢዮኤል» ማለት «እግዚአብሔር ፈጣሪ» ማለት ነው:: የይሁዳ ነቢይ ነው:: ሆሴዕ በ80 ዓመት ይቀድመዋል:: በኢዮኤል መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱ ጥቅሶች:-

ሀ.የእግዚአብሔር መዓትና የተባይ መነሳት

ለ. የንስሐ ጥሪ የእግዚአብሔር ምህረት መትረፍረፍ ስለ መጨረሻው ዘመን /Eschalogy/ ምልክቶች፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ለኹሉ ይሰጣል፣ የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ኹሉ ይድናል:: የኢዮኤል መጽሐፍ ሦስት ምዕራፍ አለው::

**<u>«ትንቢተ አብድዮ»:-</u>** «አብድዮ» ማለት «ገብረ እግዚአብሔር» ማለት ነው:: አብድዮ ከአሞፅ በኋላ 200 ዓመት ቆይቶ የተነሳ ነው:: ከብሉይ ኪዳን ውስጥ አንድ ምዕራፍ ብቻ ያለው መጽሐፍ የአብድዮ መጽሐፍ ነው:: አብድዮ ለነቢይነት የተጠራው ኢየሩሳሌም በባቢሎናውያን ከመጥፋቷ ጥቂት ቀደም ብሎ ነው:: ይኸውም በ589 ነው::/ከጌታ ልደት በፊት ነው/ የትንቢቱ ማዕከል:- ኤዶምና ይሁዳ ናቸው:: በኤዶም ላይ የጌታ ፍርድ ይመጣል:: በመጨረሻም በጌታ ቀን ኢየሩሳሌም ትቋቋማለች::

«ትንቢተ ዮናስ»፡- «ዮናስ» ማለት «ርግብ» ማለት ነው፡፡ ወደ አሕዛብ የተላከ የመጀመሪያ ነቢይ ነው፡፡ ስሟ እንደሚገልጠው ዮናስ የተላከላት ነነዌ የናምሩድ ከተማ ናት/ዘፍጥረት.10፣ 11/ ዮናስ በነቢይነት የነበረበት ዘመን ከ793 /ከጌታ ልደት በፊት / ጀምሮ ነው፡፡ ወደ ነነዌ ሔዶ እንዲያስተምር ከጌታ ትዕዛዝ ተሰጠው፣ ፈቃደኛ አልኾነም፤ በመጽሐፉ የተገለጠው፡- የዮናስ ጥሪ፡- ወደ ተርሴስ ያደረገው ሽሽት፣ ዮናስ የደረሰበት አደጋ፣ በአንበሪ ሆድ የዮናስ ጸሎት፣ የነነዌ ሰዎች ንስሐና መዳን ነበር፡፡ መጽሐፉ አራት ምዕራፍ አለው፡፡

«ትንቢተ ናሆም»፡- «ናሆም» ማለት «መጽናናት» ማለት ነው፡፡ ከዮናስ በኋላ 100 ዓመት ቆይቶ ተነሳ፡፡ በ693 /ከጌታ ልደት በፊት/ ነው፡፡ ናሆም በነነዌ የተናገረው ትንቢት 100 ዓመት ቆይቶ ተፈጸመ፡፡ በመጽሐፉ የተገለጠው፡- የእግዚአብሔር ቁጣና ጠላቱን ማጥፋት የነነዌ ክፋት የግብጽ ትዕቢት መዳኛ የሌለው መዓት በናሆም ተነግሯል፡፡ ትንቢተ ናሆም ሦስት ምዕራፍ አለው፡፡

«ትንቢተ ዕንባቆም»፡- «ዕንባቆም» ማለት «ተዋጊ» ማለት ነው፡፡ ዕንባቆም በ626/ከጌታ ልደት በፊት/ ለነቢይነት ተጠራ ትንቢቱ ከእግዚአብሔር ጋር በጥያቄና መልስ የቀረበ ነው፡፡

ሀ. ኃጢአተኞች እንዴት እንደማይቀጡ ነቢዩ እግዚአብሔር ይጠይቃል

ለ. እግዚአብሔርም ከለዳውያንን መሣሪያ አድርጎ እንደሚቀጣቸው ይመልስለታል፡፡

ሐ. ነቢዩም መልሶ እግዚአብሔር ክፉዎቹን መሣሪያ ማድረጉ ለምን እንደኾነ ይጠይቃል፡፡ ኹሉም ተያይዘው እንደሚጠፉ እግዚአብሔር ይመልስለታል፡፡ የዕንባቆም መጽሐፍ 3 ምዕራፍ አለው፡፡

«ትንቢተ ሶፎንያስ»፡- ሶፎንያስ ማለት «ስውረ እግዚአብሔር» ማለት ነው፡፡ በ627/ከጌታ ልደት በፊት/ ትንቢቱን ጀመረ፡፡ የትንቢቱ ነጥብ፡- ሀ.የእግዚአብሔር የፍርድ ቀን አለም ዓቀፋዊ መኾኑን ተናገረ፣ የእግዚአብሔር አሸናፊነት፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምና አዲስ እስራኤል፡፡ የሶፎንያስ መጽሐፍ ሦስት ምዕራፍ አለው፡፡

«ትንቢተ ሐጌ»፡- «ሐጌ» ማለት «በአሌ» ማለት ነው፡፡ ከጼዋዌ /ምርኮ/ በኋላ ከተነሱት ነቢያት የመጀመሪያ ነው፡፡ ይኸውም በ520/ከጌታ ልደት በፊት / ስለ ኢየሩሳሌም መታደስና ስለ ቤተ መቅደስ መሰራት ትንቢት የተናገረ የትንቢቱ ማዕከል፡- የመሪዎችንና ሕዝቦችን መገሰጽና ስለ በረከት ቃል ኪዳን ነበር፡፡ የሐጌ መጽሐፍ ሁለት ምዕራፍ አለው፡፡

«ትንቢተ ዘካርያስ»፡- «ዘካርያስ» ማለት «እግዚአብሔር ያሰበው» ማለት ነው፡፡ ይህ ሥም በብሉይ ኪዳን ብቻ 28 ቦታ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ዘካርያስ በማቴዎስ 23፣35 ያለው ሳይኾን በዜና መዋዕል ካልዕ 24፣20 ያለው ነው፡፡ ዘካርያስ ካህንም ነው፤ ነቢይም ነው፡፡ ዘካርያስ ስለ ጌታ መሲሐዊ ጉዞና ስለ ህማማተ መስቀሉ ተናግሯል፤ ስምንት ራዕዮችም አይቷል፡፡

ራዕይ፡-

ሀ. 1፣7-17፡፡ ስድስተኛና ሰባተኛ 5፣1-11

ለ. 1፣18-21 ስምንተኛ 6፣1-8

ሐ. 2፣1-3

መ. 3፣ 1-10

ሠ. 4፣ 1-14

ትንቢተ ዘካርያስ 14 ምዕራፍ አለው፡፡

«ትንቢተ ሚልክያስ» «ሚልክያስ» ማለት መልእክተኛዬ ማለት ነው፡፡ በ460 /ከጌታ ልደት በፊት / የነበረ ነቢይ ነው፡፡ በመጽሐፍ እንደተገለጸው የትንቢቱ አውራ ነጥቦች ፡-

ሀ. እግዚአብሔር እስራኤልን እንደሚወድ፣ እስራኤል እግዚአብሔርን እንደሚያሳዝን

ለ.ጋብቻን ለማፍረስና ሌላ ማግባት አጸያፊ ድርጊት መኾኑን፣ የወደፊት አስቃቂ ፍርድ፣ ንስሐና ከአለው ኹሉ ካሥር አንድ ለእግዚአብሔር መስጠት የሚያስገኘው በረከት፣ የእግዚአብሔር ሰዎች የወደፊት ክብር በሚልክያስ ትንቢት ተነግሯል፡፡ የሚልክያስ መጽሐፍ አራት ምዕራፍ አለው፡፡

«መጽሐፈ ዮዲት»፡- ለወገኖቿ ለእስራኤል በመቶርቆር ሆሎፍርኒስ የተባለውን ግፈኛ አንገቱን ቆርጣ የጣለች የሴት አርበኛና ጥበበኛ ናት፣ እድሜዋ 105 ዓመት ነው፡፡ መጽሐፉ አስራ ስድስት ምዕራፍ አለው፡፡

**«መጽሐፈ ጦቢት»:-** «ጦቢት» ማለት «ጤናዬ እግዚአብሔር ነው» ማለት ነው፡፡ ጦቢት በ158 ዓመቱ ዓረፈ፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የጦቢት ዓይን መጥፋት መልአኩ ሩፋኤልም ዓይኑን በዓሳ ሃሞት እንዳዳነው የራጉኤል ልጅ ሣራ የምትባለውንም ሩፋኤል መላክ እንዴት እንዳዳናት ተተርኳል፡፡ ይህ መጽሐፍ አስራ አራት ምዕራፍ አለው፡፡

**«ጥበበ ሰሎሞን»:-** ይህ መጽሐፍ የሰሎሞን ነው፡፡ ምክር ተግሳፅና እዝናትን የያዘ ነው፡፡ አስራ ዘጠኝ ምዕራፍ አለው፡፡

**«መጽሐፈ መቃብያን»:-** በ175/ከጌታ ልደት በፊት/ የነበረው አንጥያኮስ አራተኛ /አንጥያኮስ  የስሙ ትርጉም ቴዎፋኒስ ነው፡፡  ቴዎፋኒስ ማለት የእግዚአብሔር መገለጥ ማለት ነው /የአይሁድን እምነትና ባህል ለማጥፋት ብዙ ይጥር ነበር፡፡ በ167 /ከጌታ ልደት በፊት/ በሶርያ የነበረውን ምሽግ ወደ ኢየሩሳሌም አመጣው፡፡ የዚውስን ጣኦት በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ አቆመው፡፡ ሌሎችም ብዙ የአረማውያን ተግባር በቅዱሱ ቦታ መፈጸም ጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ ካህናቱ ማታትያስና ልጆቹ አልአዛር ዮናታን፣ ስምኦን፣ ይሁዳ፣ተቃዋሚ ኹነው ተነሱ፡፡ ከነዚህም በጣም ኃይለኛ የነበረው ይሁዳ ነበር፡፡ እሱም መቃቢስ የተባለው ነው፡፡ /መቃቢስ ጥይት ማለት ነው/ በ141 ከጌታ ልደት በፊት፤ከሃያ አምስት ዓመት ጦርነት በኋላ ኢየሩሳሌምን ከአንጥያኮስ አስለቀቁ፡፡ ይህ ድል የተገኘው ከማታትያስ ልጆች ባንዱ በስምኦን ነው፡፡ ሌሎቹ ግን በጦርነቱ ውስጥ አልቀዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንሦስት የመቃብያን መጻሕፍት አሏት፡፡ የመጀመሪያው መቃብያን 36 ምዕራፍ አለው፤ ኹለተኛው 21 ምዕራፍ አለው፡፡ ኹለቱ እንደ አንድ ይቆጠራሉ፡፡ ሦስተኛው መቃብያን 10 ምዕራፍ አለው /ወልደ ኮርዮስ የሚል ስምም አለው/

**«ተግሳጸ ሰሎሞን»:-** ይህ የሰሎሞን መጽሐፍ ነው፡፡ ከምሳሌ ሰሎሞን ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሰባት ምዕራፍ አለው፡፡

**«መጽሐፈ ሢራክ»:-** በአንዳንድ የጥንት መጽሐፎች «መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ሲራክ» የሚል አለ፡፡ የምክርና የጥበብ መጽሐፍ ነው፡፡ በሐዋርያት ቀኖና /አንቀጽ 85/ ለልጆቻችሁ በቅድሚያ የሢራክን ጥበብ አስተምሯቸው ተብሎ ታዟል፡፡ መጽሐፈ ሲራክ 51 ምዕራፍ አለው፡፡

**«ሄኖክ»:-** ሄኖክ ከአዳም ሰባተኛ ትውልድ ነው፡፡ /ዘፍጥ.5÷18፡፡/ የሄኖክን መጽሐፍ ሐዋርያት እየጠቀሱ አስተምረዋል /ይሁዳ. 14÷15፡፡ ዕብ.11÷5/ የሄኖክ መጽሐፍ በሥነ ፍጥረት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በተለይም  ስለ ዘመናት አቆጣጠር፣ ስለ ፀሐይና ጨረቃ ስለ ክዋክብት ስለ መላእክትም በሰፊው ያስረዳል፡፡

የሄኖክ መጽሐፍ 42 ምዕራፍ አለው፡፡ ይህ መጽሐፍ በሌሎች ቋንቋዎች ጠፍቶ በኢትዮጵያ ግዕዝ ስለተገኘ ዛሬ ተመራማሪዎች ኹሉ የኢትዮጵያ ሄኖክ እያሉ ይጠሩታል፡፡ ይህም ለቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊነት ትልቅ አስረጂ ነው፡፡

**«መጽሐፈ ኩፋሌ»:-** የቤተ ክርስቲያን አባቶች ከኦሪት የተከፈለ ስለኾነ ኩፋሌ ተባለ ይላሉ፡፡ የውጭ ጸሐፊዎች ደግሞ ይህንን መጽሐፍ የሚያውቁትና የሚያጠኑት ኢዮቤልዮ በሚል ስም ነው፡፡ በእርግጥ ይህ መጽሐፍ ከኦሪቱ የቀረውን ሁሉ አሟልቶ የበዓላቱንም የሰርቀ ወርኑንም ተራ በየረድፍ ያስቀምጣል፡፡ ሰላሣ አራት ምዕራፍ አለው፡፡

# ክፍል ሁለት
# አዲስ ኪዳን

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተመዘገበው ሐዲስ ኪዳንን ማጥናት የምንችለው በቁጥራቸው ተራ ነው። ይህም ከኾነ በማቴዎስ ወንጌል እንጀምራለን።

ወንጌል ማለት «ስብከት» ማለት ነው። «ኤቫንጌሊዮሜ» ማለት በዕርዕ ቋንቋ አዲስ ነገር መደረጉን ለሰሚው የሚጠቅም ኹኔታ መፈጸሙን መንገር ማለት ነው። ስለዚህ ወንጌል ለሚሰሙት የሰው ልጆች ኹሉ የሚጠቅም ነው። የወንጌል ስያሜ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ አለ /ኢሳ.40÷ 9። 52÷7። 61÷1። ሉቃ. 4÷18።/ ወንጌልን የጻፉት አራት ሰዎች ናቸው። ኹለቱ ከሐዋርያት /ማቴዎስና ዮሐንስ / ኹለቱ ከሰብዓ አርድዕት /ማርቆስና ሉቃስ / ናቸው። ሦስቱ ወንጌላውያን ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ የጻፉት ተመሳሳይነት አለው /Synoptic/። ዮሐንስ የጻፈው ግን ከሶስቱ የተለየ ነው። ሦስቱ ወንጌላውያን በመሲሐዊ ገጽታው ጀምረው ጽፈዋል። ዮሐንስ ግን ከቀዳማዊ ኀልውናው ጀምሮ ጽፏል። ያም ኾነ ይህ ወንጌል ስብከት እንጅ ሌላ ስላልኾነ ወንጌላውያን የጻፉት አብረው ኖረው ያዩትንና የሰሙትን ነው። የዓይን ምስክሮች ስለኾኑ ምስክርነታቸውም የታመነ ነው።

<u>«ማቴዎስ ወንጌል»</u>፡- ማቴዎስ ኹለት ስም አለው። አንዱ በወንጌሉ/ምዕራፍ 9፣9።/ ያለው ነው። የጽርዕ ስም ነው። /ዕርዓውያን ኢየሩሳሌምን በቅኝ ግዛት ይዘዋት ስለነበር ኑዋሪዎቹ በዕርዓውያን ስም ይጠሩ ነበር።/ «ማቴዎስ» ማለት በጽርዕ ቋንቋ «በእግዚአብሔር» ማለት ነው።ኹለተኛ ስሙ «ሌዊ ነው»። /ማር. 2÷14። ሉቃ 5÷ 27።/ ሌዊ ማለት «ይጠጋል» ማለት ነው። ይህ የአራማይክ ስም ነው።

ማቴዎስ የሮማውያን ቀራጭ ነበረ። ከቀራጭነት ሥራው ተጠርቶ ጌታን ተከተለ፣ ወንጌልንም ጻፈ። የማቴዎስ ወንጌል 28 ምዕራፍ አለው። ማቴዎስ ወንጌሉን የጻፈው በዕብራይስጥ ቋንቋ ነው። የጻፈበትም ቦታ በዚያው በፍልስጥኤም ነው። የጻፈበት ዘመን ከ60-68 ዓ.ም. ነው። የማቴዎስ ዕረፍት የሚከበረው ጥቅምት 12 ቀን ነው።

በማቴዎስ ወንጌል ከቀረቡት ጥቂቶች፡-

ሀ. የጌታ ሀገረ ትውልድ፡- ልደት፣ የሰባ ሰገል እጅ መንሻ፣ የንጉሡ ቁጣ፣

ለ. ጥምቀትና ጾም

ሐ. የአንቀጸ ብፁአን ስብከት በተራራው ላይ

መ. የማስተማርና የተአምራት ሥራ

ሠ. ሐዋርያትን መጥራትና ማሰማራት

ረ. ምስጢረ መንግሥት በደብረ ታቦር

ሰ. ሕማማትና ትንሣኤ ናቸው።

<u>**ለምልጃ የተደረጉ ተአምራት፡-**</u>

- ማቴ. 8፣ 5 ሮማዊ መቶ አለቃ ለልጁ አማለደ
- ማቴ. 9፣2 በአልጋ የመጣው በሽተኛ
- ማቴ. 9፣18 የኢያኤሮስ ልጅ
- ማቴ. 15፣22 የከነናዊቷ ልጅ
- ማቴ 17፣14 የሚጥል በሽታ የያዘው ልጅ በአባቱ አማላጅነት ድኗል።

የሐዋርያት ቁጥር 12 መሆኑ በዚህ ወንጌል ተገልጧል። ማቴ 10፣1-4

| | |
|---|---|
| 1. ጴጥሮስ | 7. በርተሎሜዎስ |
| 2. እንድርያስ | 8. ቶማስ |

3. ያዕቆብ
4. ዮሐንስ
5. ፊልጶስ
6. ስምኦን /ቀነናዊ/
9. ማቴዎስ
10. ያዕቆብ /ወልደ እልፍዮስ/
11. ታዴዎስ /ልብድዮስ/ ይሁዳ/ዮሐ. 14÷22::/
12. ይሁዳ/ በኋላ ማትያስ/

**በምዕራፍ 25 ቁጥር 35- 36 የምግባር ዋጋ:-**

1. ተርቤ አብልታችሁኛልና
2. ታርዤ አልብሳችኹኛልና
3. ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና
4. እንግዳ ሁኜ ተቀብላችሁኛልና
5. ታምሜ ጠይቃችሁኛልና
6. ታስሬ ወደኔ መታችኋልና

**ወደኔ ኑ:-የሥነ ሕይወት ትምህርት (ማቴ 5፤ 1-2)**

1. በመንፈስ ድሆች ብፁአን ናቸው::/ብፁዕ ማለት በእግዚአብሔር ዘንድ የከበረ ማለት ነው::/
2. የሚያዝኑ » »
3. የዋሆች » »
4. ስለ ጽድቅ የሚራቡ » »
5. ለሰው የሚራሩ » »
6. ልቡናቸው ንጹህ የሆነ ብፁአን ናቸው::
7. የሚያስታርቁ ብፁአን ናቸው::
8. ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁአን ናቸው::

**የክርስቲያን ሥነ ምግባር ማቴ 5፤21:: ም.7፤5:**

1. ወንድምን አለመቆጣት
2. ወንድምን አለመስደብ
3. ፈጥኖ መታረቅ
4. ዓይንን ወደ ዝሙት አለመላክ
5. ጋብቻን አለማፍረስ
6. አለመማል
7. ክፉን በክፉ አለመቃወም
8. ጠላትን መወደድ
9. ከውዳሴ ከንቱ ምጽዋት መራቅ
10. ከውዳሴ ከንቱ ጸሎት መራቅ
11. ከውዳሴ ከንቱ ጦም መራቅ
12. ስለ ገንዘብ ጠቃሚነትና ጎጂነት
13. በሰው መፍረድ እንደማይገባ::

በቤተክርስቲያን በምንማረው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ያልገባን ካለ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ሲያያዝ የመጣውን ሐዋርያዊ ትውፊት ከመምህራን ጠይቀን መረዳት እንጅ ራሳችን በፈቃዳችን ግምት መስጠት አይገባም:: ወይም በተሳሳተ አመለካከት የተሳሳተ ግምት የሚሰጡ ደፋር ጥራዝ ነጠቆች የሚሉትን መከተል የለብንም:: የእግዚአብሔር መንፈስ በመምህራን አድሮ የሚያረካን መልስ እስኪሰጠን ድረስ ደጅ መጥናት አለብን:: ይህ ካልሆነ አደጋ ላይ እንወድቃለን:: ደጅ ጥናታችንም በጸሎት ነው::

በማቴዎስ ወንጌል ቢጽ ሐሳውያን ለክርክር ከሚጠቀሙባቸው ጥቂቶቹ፡-

ማቴ 1 ፥ 25::፣ 13 ፥ 55:: በእነዚህ ቁጥሮች ያሉትን ንባቦች ይዘው ፀረ ማርያሞች የእመቤታችንን ዘለአለማዊ ድንግልና በማስተባበል ጌታ ሌሎች ወንድሞች እንዳሉት በድፍረት ይናገራሉ:: የቤተ ክርስቲያን እምነት በእልክና በበቀል የሚኾን አይደለም:: በእግዚአብሔር መንፈስ ጥላ ሥር ኹኖ በማጥናት ነው እንጅ::

በመሠረቱ «የበኩር ልጅ» ማለት በግድ ከሱ በኋላ ሌላ ልጅ መኖር አለበት ማለት አይደለም:: የመጀመሪያም የመጨረሻም ያው አንዱ ይኾናል:: በብሉይ ኪዳን በኩር ማለት የቤተሰብ እልቅና እና ኹለት እጅ የመካፈል መብት ነው:: /ዘዳግ 21÷ 17::/ ብኩርና በዋጋም ይሸጣል/ዘፍጥ. 25÷31-34:: ዕብ.12÷ 16::/ በኃጢአትም ምክንያት ይነጠቃል:: የሮቤል ብኩርና እንደተወሰደበት /ዜና. መዋ. ቀዳ. 5÷1-3/ እግዚአብሔር ለፈቀደለትም ትልቁ ሳለ ለትንሹ ይሰጣል ምናሴ እያለ ለኤፍሬም ተሰጥቷል:: /ዘፍጥ.48÷ 14-20/ ብኩርና በትውልድ ቅድሚያም ይኾናል::/ዘፀ.12÷29-30:: ዕብ 11÷28::/

በእምነታቸው ጥንካሬ እግዚአብሔር እስራኤልን የበኩር ልጄ ይላቸው ነበር /ዘፀ.4÷ 22::/ በክርስቶስ ያመኑ ምዕመናንን ኹሉ በኩራት ይላቸዋል::/ዕብ 12÷23::/ ዳዊትም በመዝሙሩ ስለ መሚሕና መሚሐውያን ትንቢት ተናግሯል::/መዝ. 88÷ 27::/ በምሥጢረ ሥጋዌ /በፍና ትስጉት/ «በኩር» ማለትና «ወልድ ዋሕድ» ማለት አንድ ነው:: በሥጋዌው «በኩረ ድንግል» የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ በቀዳማዊ ልደት «በኩረ አብ» ነውና እንደ ቢጽ ሐሳውያን አባባል ከኾነማ አብም በቅድምና ሌሎች ልጆች ነበሩት ያሰኛል::

በመሰረቱ ማቴዎስና ሉቃስ «የበኩር ልጇ» ብለው የሰየሙት ወልድ ዘለዓለማዊ አምላክ ነው እንጅ ተራ ሰው አይደለም:: ብኩርናው የገዢነት፣ የመጋቢነት እንጅ የመወለድ አይደለም:: ቅድመ ዓለም ከአብ ተወልዷልና:: «የበኩር ልጇን እስከምትወልድ አላወቃትም» ማለት ወላዲተ አምላክ ትኾናለች ብሎ አላወቀም ነበር ማለት ነው:: ሐዋርያዊ አባት ሔሬኔዎስ እንዳለውም «እስከ» የሚባለው ንባብም ፍጻሜ የሌለው ነው:: «የጥፋት ውሃ እስኪደርስ ድረስ ኖህ የላከው ቁራ አልተመለሰም» እንደ ማለት ነው:: ይህም ማለት ውሃው ከደረቀ በኋላም ቁራው አልተመለሰም::

ስለ ብኩርና በተጨማሪ:- ጌታ ከዚህ ሌላ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሦስት ጊዜ «በኩር» በሚል ቅጥል ተጠርቷል::

1. /ቆላስ 1÷15-16::/ የፍጥረት ኹሉ በኩር መኾኑን ቅዱስ ጳውሎስ ገልጧል:: ይህም ማለት የፍጥረታት ገዢ ማለት ነው::
2. በኩረ ትንሳኤ፡ የትንሣኤ በኩር ተብሏል/ቆላስ 1÷18:: ራዕ 1÷5::/ ዳግም ሞት የሌለበት የምዕመናንን ትንሣኤ ያሳየ ማለት ነው::
3. በኩረ ምዕመናን:- የምዕመናን አለቃ ተብሏል::/ሮሜ. 8÷29::/ ምዕመናን ከሱ የተሰጠቸውን ክብር ለብሰው እሱን መሪ አድርገው ወደ መንግሥቱ የሚገቡ መኾናቸውን ለመግለጥ ነው:: እንግዲህ ቅዱሳት መጻሕፍትን የምናጠናው ለመረዳት በሚስማማ መንገድ ነው::

<u>**«የማርቆስ ወንጌል»:-**</u> ኹለተኛው ወንጌል የተጻፈው በማርቆስ ነው:: የማርቆስ ኹለተኛ ስሙ ዮሐንስ ነው/ማርቆስ የላቲን ስሙ ነው፣ ዮሐንስ አራማይክ ነው::የሐዋ.12÷25::/ ማርቆስ በአዲስ ኪዳን ስምንት ጊዜ ተወስቷል:: ጴጥሮስ ማርቆስን «ልጄ» ይለው ነበር/ቀዳ. ጴጥ 5÷13/

ቅዱስ ጳውሎስም የቅዱስ ማርቆስን ሐዋርያዊ አገልግሎት ያደንቅ ነበር /ካል.ጢሞ 4÷11::/ በራሱ በማርቆስ ወንጌል እንደተገለጠው ውሃ በማድጋ ተሸክሞ ሲሄድ ሐዋርያት ያገኙት፣ ጌታም የፋሲካን በዓል በሱ ቤት እንዲያከብር ቤቱን እንዲያዘጋጅ የነገረው ሰው ይህ ማርቆስ ነው:: /ማር. 14÷12-16::/ ጌታም በተያዘ ጊዜ ያንገት ልብሱን /ሻሎን/ ባንገቱ ላይ ጠምጥሞ የተከተለው ይኸው ማርቆስ ነው:: /ማር. 14÷51-52/ የማርቆስ እናት የማርያም ቤት ኹል ጊዜ የሐዋርያት መሰባሰቢያና መጸለያ ነበር:: /የሐዋ. ሥራ 12÷12::/ በኋላም መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉበት ቤት ይኸው የማርቆስ እናት ቤት ነው::/ሐዋርያት ከዕርገት እስከ ጰራቅሊጦስ የነበሩት በዚሁ ቤት ውስጥ ነበር፣ ይህን ቤት ቲቶ ኢየሩሳሌምን ሲያጠፋ አላፈረሰውም ይባላል፡፡ **Epiphonius, de Mens. Etpond.14, Cyril Jerusalem. Catech. 16**::/ ቅዱስ ማርቆስ በግብጽ ሐዋርያዊ ተልእኮውን ፈጽሞ ትምህርት ቤት አቋቁሞ በ66 ዓ.ም በግፈኞች ሰዎች ጥላቻ በበሬ ጅራፍ ታስሮ ደንጊያ ለደንጊያ እየተጎተተ ተቆራርጦ በሰማዕትነት ሙቷል::

ቅዱስ ማርቆስ ቁጥሩ ከሰብዓ አርድዕት ነው:: እረፍቱ የሚከበረው ሚያዝያ 30 ቀን ነው:: በማርቆስ ወንጌል የተመዘገቡት ነጥቦች በማቴዎስ ወንጌል ካሉት ጋር ይገናዘባሉ:: ማርቆስ በጌታ ጥምቀት ወንጌሉን ይጀምራል::

1. የጌታ ጥምቀትና ጾም፣

2. የጌታ የማስተማርና የተአምራት ሥራ፣
3. ሕማማት፣ ትንሣኤና ዕርገት፣
4. የጥምቀት አዳኝነት::

የማርቆስ  ወንጌል አስራ ስድስት ምዕራፎች አሉት::

**«<u>የሉቃስ ወንጌል</u>»:-** ሉቃስ በአንጾኪያ የተወለደ የግሪክ ሰው ነው:: ቅዱስ ሉቃስ በዘመኑ የነበረውን የሕክምና ሙያ ያጠና የሕክምና ዶክተር ነው:: / ቆላስ. 4÷14:/ ሉቃስ ከጳውሎስ ጋር ሐዋርያነት ተባባሪ ነበር /ፊልሞና 2 ፥ 4::/ ዴማስ ይህን ዓለም ወዶ ጳውሎስን ከድቶ በሔደ ጊዜ ቃል ኪዳኑን ጠብቆ ከጳውሎስ ጋር የቆየ ይኸው ሉቃስ ነበር /ካል. ጢሞ 4÷11::/ የትንሣኤ ዕለት ወደ ኤማሁስ ሲሄድ ካነጋገራቸው ኹለት ሰዎች አንዱ ቀለዮጳ ኹለተኛው ሉቃስ መኾኑ በቤተ ክርስቲያን ታሪክና ትውፊት ይነገራል/ስሙን አለማንሳቱ ጸሐፊው ራሱ ስለኾነ ነው::/ሉቃ24፣13-27/ ሉቃስ ከወንጌሉ ሌላ የሐዋርያት ሥራን ጽፏል::  የሉቃስ ቁጥሩ ከሰብዓ አርድእት ነው::/ከአሥራ ኹለቱ ሐዋርያት ሌላ ሰብአ ተጨማሪ አርድእት መመረጣቸውንም ይህ ወንጌላዊ ገልጧል:: / ሉቃ 10፣1::/

**በሉቃስ ወንጌል የሠፈሩ ነጥቦች**

ሀ. የዮሐንስ መጥምቅ ልደት፣

ለ. የቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ወደ እመቤታችን፣

ሐ. የጌታ ልደት

መ. የመላእክትና የእረኞች ምስጋና፣

ሠ. የጌታ ትምህርትና ተአምራት፣

ረ. ሕማማት፣ ትንሣኤና ዕርገት::

**በማቴዎስና በማርቆስ ከተመዘገቡት የተለዩ ስድስቱ የሉቃስ ወንጌል ተአምራት**

1. የዓሣው ድርቅ/5 ፥ 11/
2. በናይን ያስነሳው ወልደ መበለት /7 ፥ 11/
3. ጎባጣዋ ሴት /13 ፥ 11/
4. ሆዱ የተነፋው ሰው /14 ፥ 1/
5. አሥሩ ለምጻሞች /18 ፥ 11/
6. የማልኮስ ጆሮ መቀጠል:: /22 ፥ 50/

***በማቴዎስና በማርቆስ ከተመዘገቡት የተለዩ የሉቃስ ምሳሌዎች አስራ አንድ ናቸው::***

1.ኹለት ተበዳሪዎች/7 ፥ 41/

2. መልካሙ ሳምራዊ/10 ፥ 30/

3. የማይሰላች ወዳጅ/11 ፥ 5/

4. ስግብግብ ባለጠጋ /12 ፥ 16/

5. መካን የበለስ ዛፍ/13 ፥ 6/

6. የጠፋው የብር መሐለቅ /15 ፥ 8/

7. አባካኙ ልጅ /15 ፥ 11/

8. ብልጡ መጋቢ /16 ፥ 1/

9. ጨካኙ ባለጠጋና ድሃው/16 ፥ 19/

10. የማትሰለች መበለት /18 ፥ 1/

11. የፈሪሳዊና የመጸብሐዊ ጸሎት /18 ፥ 9/::

«የዮሐንስ ወንጌል»:- ዮሐንስ የያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ ወንድም ነው:: ዮሐንስና ወንድሙ ያዕቆብ ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋር ኹነው በገሊላ ባህር ዓሣ ሲይዙ ለሐዋርያነት ተጠሩ:: እነሱም ቃሉ ወደ ጆሯቸው እንደደረሰ አፈፍ ብለው መረባቸውንም አባታቸው ዘብዴዎስንም ትተው ተከተሉት:: /ማቴ. 4÷21-22/

ዮሐንስና ያዕቆብን ጌታ «ቦአናርጌስ»ብሎ ሰይሟቸዋል «ደቂቀ ነጎድጓድ» ማለት ነው:: በምስጢር ግን መብረቅ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ አንድ ጊዜ እንደሚታይ የወንጌልንም መልእክት በዚህ አይነት የሚያደርሱ ማለት ነው:: /ማር. 3÷17::/ የዮሐንስና የያዕቆብ እናት ማርያም የእመቤታችን ዘመድ ናት:: ስለዚህም ወደ ጌታ ጠጋ ብላ እነዚህ ሁለቱ ልጆቿ በቀኝና በግራው በሥልጣን እንደሚቀመጡላት ለመነች/ማቴ 20÷20::/

ይህን አራተኛውን ወንጌል የጻፈው ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ ነው:: «ዮሐንስ» ማለት «ደስታ» ማለት ነው:: በወንጌሉ ውስጥ ስሙን እያነሳም «ሌላው ረድእ» «ጌታ የሚወደው ሌላው ረድእ» ከማለት በቀር:: /ዮሐ 20÷3-4:: 13÷23:: 21÷7::/ዮሐንስ ከወንጌሉ ጋር አምስት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ጽፏል::/ወንጌሉ፣ሦስት መልዕክታት፣ራዕይ::/

ከጸሎተ ሐሙስ ማታ ዕለት ጀምረው ሐዋርያት ጌታን ትተውት በሸሹ ጊዜ ዮሐንስ አልተለየውም ነበር:: በመስቀሉም አጠገብ ከእመቤታችን ጋር ቁሞ ሳለ ዘመድ ስላልነበራት በመስቀል ላይ ጩኸ ከተናገራቸው ከሰባቱ አንዱ ጌታ እናቱን እንዲጠብቅለት አደራ ሰጠው::/ዩሐ.19÷26::/

ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና እንዲረዳችሁ ጌታ በመስቀል ላይ ጩኸ አሰምቶ የተናገራቸውን ዐረፍተ ነገሮች አጥኑ፣በግዕዝ ሰባቱ አጽራሃ መስቀል ይባላሉ::

1. አባቴ ሆይ የሚሰሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው /ሉቃ23 ፥ 34::/
2. እነኾ ልጅሽ እነኋት እናትህ / ዮሐ 19 ፥ 26/
3. ዛሬ ከኔ ጋር በገነት ትኾናለህ/ሉቃስ 23 ፥ 43/
4. ተጠማሁ /ዮሐንስ 19 ፥ 28/
5. አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ/ማቴ27 ፥ 46/
6. ኹሉም ተፈጸመ /ዮሐ 19 ፥ 30/
7. አባቴ ነፍሴን በእጅህ አደራ ብያለኹ /ሉቃ 23 ፥ 46::/

ዮሐንስ ብዙ ያስተማረው በኤፌሶን ነው:: በኤፌሶን ሳለ ለድምጥያኖስ ጣኦት እንዳይሰገድ ከልክሎ በዚህ ምክንያት ተግዞ በኤጂያን ባህር ውስጥ በምትገኝ ፍጥሞ በምትባል ትንሽ ደሴት ተግዞ ይኖር ነበር:: በዚህ ደሴት ሳለ ነው የሐዲስ ኪዳን የመጨረሻውንና የትንቢት መጽሐፍ ራዕዩን ያየውና የጻፈው:: በቤተ ክርስቲያን ዮሐንስ ብዙ ቅጥሎች አሉት::

ሀ. ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ

ለ. ዮሐንስ ታዖሎጎስ

ሐ. ዮሐንስ ወንጌላዊ

መ. ዮሐንስ ድንግል

ሠ. ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ

ረ. ዮሐንስ አቡቀለምሲስ

ሰ. ዮሐንስ ዘረፈቀ ውስተ ሕፅኑ ለኢየሱስ ይባላል::

ስለ ዮሐንስ ዕድሜና ሞት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚባለው ጴጥሮስ ስለ ዮሐንስ ጌታን በጠየቀው ጊዜ እኔ እስከምመጣ ድረስ ቢቆይ አንተ ምን ቸገረህ አለው:: በዚህም መነሻ ዮሐንስ በኤፌሶን እንዳለ ተሰወረ እንጅ እንደሌሎች ሐዋርያት በዚያ ቦታ ሞተ

ተብሎ አልተነገረም /ዮሐ. 20÷ 20-23/። አንዳንድ ጊዜም ከተሰወረ በኋላ መቋሚያውንና ሌሎቹንም የቀበሩበትን እንደ ሞቱና መቃብሩ አድርገው የሚተርኩት አሉ። የተሰወረበት በዓሉ ግን የሚከበረው ጥር 4 ቀን ነው።

***በሦስቱ ወንጌሎች ያልተገለጡ በዮሐንስ ወንጌል ያሉ ተአምራት፡-***

1. የቃና ሠርግ /2 ፥ 1/
2. የገዢ ልጅ መዳን /4 ፥ 46/
3. የመጻጉዕ መዳን /5 ፥ 1/
4. የዕውሩን ግንባር ጭቃ ቀብቶ ዐይን መፍጠር /9 ፥ 1/
5. የአልዓዛር ትንሳኤ /11 ፥ 1፡፡/
6. የዓሣው መገኘት በጥብርያዶስ /21 ፥ 1/
7. በዝግ ቤት መግባት ራሱን ለቶማስ መግለጥ /ዮሐ 20 ፥ 19 - 29፡፡/

**በዚህ ወንጌል አምስት የፋሲካ በዓላት አሉ።**

1. ዮሐንስ 2 ፥ 13፡፡
2. ዮሐንስ 5 ፥ 1፡፡
3. ዮሐንስ 6 ፥ 4፡፡
4. ዮሐንስ 7 ፥ 2፡፡
5. ዮሐንስ 12 ፥ 1፡፡

የዮሐንስ ወንጌል ማዕከሉ የወልድ ኅልውና ከሥጋዌ በፊት ነው ብሎ ማስረዳት ሲሆን ይህ መንጌል ከሶስቱ «በዘኅብሩ» ከሚባሉት ወንጌሎች /Symptic/ በቃላት የተለየ ይኹን እንጅ አንድ ነው፡፡ ወንጌሉ የሚያስተምረው ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አብ ወልደ ማርያም መኾኑንና ዓለም አምኖ እንዲድንበት ነው፡፡ የዮሐንስ ወንጌል ዛያ አንድ ምዕራፍ አለው፡፡

*«<u>የሐዋርያት ሥራ</u>»፡-* የሐዋርያት ሥራን የጻፈው ወንጌላዊው ሉቃስ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ዋና ዋና ነጥቦች፡-

*ሀ.* የጌታ ዕርገትና የሐዋርያት ጉባኤ፣

**ለ.** በይሁዳ ፈንታ የማትያስ መመረጥ፣

*ሐ.* የመንፈስ ቅዱስ ስጦታና የቤተ ክርስቲያን የልደት ቀን፣

*መ.* የቤተ ክርስቲያን ስደት ለመስፋፋት መጥቀሙ፣

*ሠ.* የቅዱስ ጳውሎስ መማረክ፣

*ረ.* በአንጾኪያ የተቋቋመችው ቤተ ክርስቲያን ለሐዋርያት መናኸሪያ መኾኗ፣

*ሰ.* ደቀ መዛሙርት ይባሉ የነበሩት ለመጀመሪያ ጊዜ በአንጾኪያ ክርስቲያን መባላቸው/የሐ. ሥራ 11÷26፡፡/አንጾኪያ ከጌታ ልደት በፊት በ301 ዓመት ተመሠረተች፡፡ የመሠረታትም ሴሌውኮስ ኒክቶር የተባለ የአንጥያኮስ ልጅ ነው፡፡ ይህ መሪ በአባቱ በአንጥያኮስ ስም አሥራ ስድስት ከተሞችን አንጾኪያ ብሏቸዋል፡፡ የሶርያ ዋና ከተማ የነበረችው ይህች አንጾኪያ አስራ ስድስተኛ ይቱ ናት፡፡ ከጌታ ልደት በፊት በ83 ዓመት አርመኖች ይዘዋት ነበር፡፡ አሥራ አራት ዓመት እንደያዟት እነሱን አስለቅቀው ሮማውያን ያዟት፡፡ የብዙ ሕዝብ መኖሪያና የንግድ ማዕከል የነበረችው አንጾኪያ የምስራቅ እቴጌ The Queen of the East ትባል ነበር፡፡/

በዚህ መጽሐፍ የተገለጠው የቅዱስ ጳውሎስ ጉዞ:- ከሶስት ይከፈላል።

1. የመጀመሪያው ጉዞው ወደ አንጾኪያ፣

   የሐዋርያት ሥራ ምዕ 13 እስከ 18 ቁጥር 23።

2. የኤጂያን /የኤፌሶን/ ጉዞ:-

   የሐዋ ሥራ ምዕ 18 ቁጥር 24 እስከ 21 ቁጥር 10

3. የምርኮው ጊዜ:-

   የሐ. ሥራ. ምዕ 21 ቁ 11 እስከ ምዕራፍ 28።

   የሐርያት ሥራ 28 ምዕራፍ አለው።

## <u>የቅዱስ ጳውሎስ 14 መልእክታት</u>

ቅዱስ ጳውሎስ:- የቅዱስ ጳውሎስ ዕብራዊ ስሙ ሳውል ነው ሳውል/ሳኦል/ማለት በልመና የተገኘ/ዘተስእለ/ ማለት ነው። ጳውሎስ ግን ሮማዊ ስሙ ነው። ከነገደ ብንያም በጠርሴስ የተወለደ ፈሪሳዊ ነበር። እስጢፋኖስ በተገደለ ጊዜ ተባባሪ ነበር። በኋላ በደማስቆ መንገድ እግዚአብሔር በተአምራት ማረከው። የክርስቲያን ጠላት የነበረው ጳውሎስ ክርስቲያን ኾነ። የቤተ ክርስቲያን ሐዋርያ ኾነ። ብዕር ቀርጦ ቀለም በጥብጦ ብራና ፍቆ አሥራ አራት የክርስትና ማስተማሪያ መጻሕፍትን በመንፈስ ቅዱስ እየተቃኘ ጻፈ። በማስተማር ጊዜው ብዙ ጊዜ ታስሯል ተደብድቧል። በየአደባባዩ እየተከሰሰ መከራ ተቀብሏል። በመጨረሻም ሐምሌ አምስት ቀን 64 ዓ.ም. በኔሮን ቄሳር ትዕዛዝ አንገቱን በሰይፍ ተቆርጦ በሰማዕትነት ሙቷል። ቅዱስ ጳውሎስ በኋላ ያመነ ቢኾንም ምርጥ ዕቃ ብሎ ጌታ የተናገረለት ስለኾነ ሐዋርያ ነው። በርእሰ ከተማችን በአዲስ አበባ የቅዱስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን አለ።

### 1. <u>ወደ ሮም ሰዎች</u>

ይህ መልእክት የተጻፈው በቆሮንቶስ ነው። ይህ መልእክት ወደ ሮም ሲላክ በሮም ሐዋርያ የነበረ አይመስልም። ቢኖር ኑሮ ቅዱስ ጳውሎስ ስሙን ይጠራው ነበር። የክርስቲያን ማኅበር ግን ነበር። ክርስትና ወደ ሮም የገባው በልዩ ልዩ ኀብኝዎችና በተለይም በበዓለ ሃምሳ ከየሃገሩ ተሰብስበው የነበሩ ሰዎች የሐዋርያትን ስብከት ሰምተው ክርስትናንም ተቀብለው ወደየሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮም የገባው በ60 ዓ.ም ገደማ ነው። ያን ጊዜ የሮም ሕዝብ ብዛት ከአንድ ሚሊዮን ተኩል እስከ ኹለት ሚሊዮን ይደርስ ነበር፤ በኋላም ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር በሰማዕትነት የሞተው በሮም ነው።

በዚህ መልእክት ውስጥ የሰፈሩት መመሪያዎች:-

   ሀ. የወንጌል መመሪያ

   ለ. የክርስቲያኖች ሥነ ሕይወት

   ሐ. ቤተ ክርስቲያንና ሕግ

   መ. የአይሁድ የመብት ጥያቄ

   ሠ. ክርስትና እና ግዴታው

   ረ. ለክርስቲያኖች ሰላምታ ናቸው። ይህ መልዕክት አስራ ስድስት ምዕራፍ አለው።

### 2. <u>የመጀመሪያይቱ የቆሮንቶስ መልእክት:-</u>

ቆሮንቶስ በግሪክ ደቡብ የምትገኝ የንግድ ከተማ ነበረች። ቅዱስ ጳውሎስ ወደዚች ከተማ የገባው በ50 ዓ.ም ገደማ ነው። በዚች ከተማ አንድ ዓመት ከመንፈቅ ሲያስተምር ቆይቷል/የሐ.ሥራ 18÷ 11-18/ ባንድ ቦታ ላይ ይህን ያህል መቆየት በጳውሎስ ዘንድ ያልተለመደ ቢኾንም የእግዚአብሔርን መመሪያና ትዕዛዝ ለማክበር ነው።/የሐ. ሥራ 18÷ 9-10።/

በዚህ መልዕክት ውስጥ የሰፈሩ ነጥቦች

ሀ. የመግቢያ ሰላምታ

ለ. የክርስቲያኖች መለያየት

ሐ. የክርስቲያኖች ጋብቻ

መ. የሥነ ምግባር ብልሽት

ሠ. የክርስቲያኖች ፍቅር፣ ነጻነትና ክልሉ

ረ. ስለ ሙታን ትንሳኤ ናቸው። ይህ መልእክት አስራ ስድስት ምዕራፍ አለው።

**3. ኹለተኛው የቆሮንቶስ መልእክት**

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው የመጀመሪያው ከተጻፈ ከአንድ ዓመት በኋላ ነው። በዚህ መልዕክት ዋናዎቹ ነጥቦች፡-

ሀ. የቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያዊ አገልግሎት

ለ. ለኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች ከክርስቲያን የቆሮንቶስ ወንድሞቻቸው የተላከ የአስተዋጽኦ ርዳታ

ሐ. የቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያዊ ሥልጣን ናቸው። ካልዕ ቆሮንቶስ አስራ ሦስት ምዕራፍ አለው።

**4. የገላትያ መልእክት፡-**

ከጌታ ልደት በፊት 300 ዓመት ቀደም ብሎ ሴልቲክ/Celtic/ የሚባሉ ጉሳዎች ይኖሩባት የነበረች በታናሽ ዕስያ የምትገኝ አገር ናት። ሰሜን ገላትያ እና ደቡብ ገላትያ በመባል የታወቀች ናት። በዚች አገር የነበሩ ክርስቲያኖች/የተጠመቁት/ የተመሠረቱት በራሱ በቅዱስ ጳውሎስ ነው። በዚህ መልዕክት ውስጥ ዋናዎቹ ነጥቦች፡-

ሀ. ታሪክ ለ. እምነትና ሕግ ሐ. ምክር ናቸው። የገላትያ መልዕክት ስድስት ምዕራፍ አለው

**5. የኤፌሶን መልዕክት፡-**

ኤፌሶን በታናሽ እስያ ምዕራብ የምትገኝ ከተማ ናት፤ ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶንና በአካባቢዋ ባሉ መንደሮች ከኹለት ዓመት በላይ ቆይቷል።/የሐዋ.ሥራ 19÷ 8-10።/ ከኢየሩሳሌም መውደቅ በኋላ ኤፌሶን ዝነኛ የክርስቲያኖች ከተማ ኹና ነበር።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክም በቅዱስ ቄርሎስ የተመራው ጉባኤ የተሰበሰበውና ንስጥሮስን ያወገዘው በኤፌሶን ነው።/በ431 ዓ.ም /

የኤፌሶን፣ የቆላስዮስ፣ የፊልጵስዮስና የፊልሞና መልዕክታት የተጻፉት ቅዱስ ጳውሎስ በእስር ቤት ሳለ ነው። እነዚህ አራቱ የቅዱስ ጳውሎስ የእስር ቤት መልእክታት ይባላሉ። የኤፌሶን መልእክት ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ሰላምታ

ለ. ለቤተ ክርስቲያን ስለ ተሰጠው ፀጋ

ሐ. እግዚአብሔርን ማመስገን፣

መ. የመልእክቱ አንባቢዎች በመንፈስ ቅዱስ እንዲያድጉና እንዲጠነክሩ

ሠ. የክርስቲያኖች ውጊያ ናቸው።

የኤሶን መልዕክት 6 ምዕራፍ አለው።

**6. የፊልጵስዮስ መልእክት፡-**

ይህች ከተማ /በ316 ከጌታ ልደት በፊት/ በታላቁ እስክንድር አባት በፊልጶስ ተመሰረተች። ስያሜዋንም ያገኘችው በሱ ስም ነው። የፊልጵስዮስ ቤተ ክርስቲያን የተመሰረተችው በራሱ በቅዱስ ጳውሎስ ነው። /የሐዋ. ሥራ 16÷ 12-40።/

በዚህ መልእክት ውስጥ የተመዘገቡ ነጥቦች፡-

ሀ. ሰላምታ፡- የጳውሎስ የእስራት ውጤት

ለ. ክርስቶስ ያለበትን ሰማያዊ አገር ምዕመናን እንዲያስቡ የቅዱስ ጳውሎስ ጥሪ ናቸው። ይህ መልዕክት አራት ምዕራፍ አለው።

**7. የቈላስይስ መልዕክት:-**

ቈላስዩስ በኤፌሶን ምሥራቅ የምትገኝ የክርስቲያኖች መናኸሪያ ከተማ ነበረች።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምናያቸው:-

ሀ. የመልዕክታቱ መጀመሪያ የተለመደው የቅዱስ ጳውሎስ ምስጋና ጸሎት፣

ለ. የጌታ መገለጥ፣

ሐ. የሐዋርያት አገልግሎት፣

መ. ምዕመናን የመናፍቃንን ትምህርት እንዳይቀበሉ ምክር ናቸው።

የቆላስዮስ መልዕክት አራት ምዕራፍ አለው።

**8. የተሰሎንቄ መልዕክት/ቀዳማዊ/**

ተሰሎንቄ የመቄዶንያ ከተማ ናት። መጀመሪያ ስሟ «ቴርም» /በአካባቢዋ ፍል ውሃ ስላለ ነው «ቴርሞስ» ሙቅ ማለት ነው።/ ይባል ነበር፤ በ315 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት የነበረው ካሳንደር የተባለው ንጉሥ በባለቤቱ ስም «ቴሳሎኒኪ» ተሰሎንቄ ብሏታል።/የታላቁ እስክንድር እህት ናት።/

በተሰሎንቄ መልዕክት የምናነበረው:-

ሀ. ሰላምታና እግዚአብሔርን ማመስገን፣

ለ. ስለ ዳግም ምጽአት

ሐ. ቡራኬና ጸሎት፣

መ. የመጨረሻ የስንብት ሰላምታ። ይህ መጽሐፍ አምስት ምዕራፍ አለው።

**9. የተሰሎንቄ መልዕክት/ካልዕ/:-**

እንደ መጀመሪያው መልዕክት ይህም የተላከው ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ነው። ዋናዎቹ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ምዕመናንን በማባበል ማጠናከር፣

ለ. በቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዓት አስፈላጊነት፣

ሐ. የሐሳዊ መሢሕ አመጣጥ

መ. ጸሎተ ቡራኬና የመጨረሻ ሰላምታ። ይህ መጽሐፍ ሦስት ምዕራፍ አለው።

**10. ወደ ጢሞቴዎስ የተላከ መልዕክት/ ቀዳማዊ/:-**

ጢሞቴዎስ የተወለደው በልስጥራን ደርቤን ነው /የሐዋ. ሥራ16÷1። ልስጥራን ወይም ደርቤን አሁን በዘመናዊቷ ቱርክ ውስጥ ይገኛሉ።/። እናቱ አይሁዳዊት ናት አባቱ ግን አረማዊ ነበር። የብሉይ ኪዳን እምነት ከእናቱና ከአያቱ ሲማር ያደገ ነው።/ካልዕ ጢሞ 1÷5። 3÷14-15።/ ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ሊያስከትለው በጠራው ጊዜ በጊዜው በአካባቢው የነበሩ አይሁድ ይህን የጠብ ምክንያት እንዳያደርጉ እስከዚያ ቀን ድረስ ጢሞቴዎስ አልተገረዘም ነበር።/የሐዋ.ሥራ 16÷3።/ ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን «ልጄ»ይለው ነበር። /ቀዳ. ቆሮ 4÷14-17።/ ኋላም በኤፌሶን ያለችውን ቤተ ክርስቲያን እንዲመራ ኤጲስ ቆጶስነት ሾሞታል /ቀዳ. ጢሞ1፣/ በመጨረሻም ጢሞቴዎስ በሰማዕትነት አረፈ።/Eus. HE lll. Iv 61,/

ቀዳማዊ ጢሞቴዎስ፣ ካልዕ ጢሞቴዎስና ቲቶ ሦስቱ መልዕክታት የግብረ ኖሎት መልዕክታት ይባላሉ። የቤተ ክርስቲያን ካህናትና ጳጳሳት ምዕመኖቻቸውን እንዴት እንደሚመሩና እነሱም ራሳቸው ምን ዓይነት መኾን እንደሚገባቸው መመሪያ የሚሰጡ መልዕክታት ናቸው። በዚህ የምናጠናቸው

ሀ. ጸሎትና የትምህርት መመሪያ፣

ለ. ስለ ምዕመናን ሴቶች የኑሮ ዓይነት፣

ሐ. ስለ ቀሳውስትና ዲያቆናት ምርጫ፣

መ. ስለ ኋለኛው ትውልድ መበላሸት የጳውሎስ ትንቢት፣

ሠ. በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ስለሚሰጡና ስለሚጦሩ አረጋውያንና ለጢሞቴዎስና ለቤተ ክርስቲያን ስለተሰጠው አደራ።

ይህ መልዕክት ስድስት ምዕራፍ አለው::

**11. ካልዕ ጢሞቴዎስ:-**

ትምህርቱና መመሪያው እንደፊተኛው እንደ አንደኛ ጢሞቴዎስ ነው:: በዚህ መልዕክት ውስጥ ተጨማሪው ነጥብ:-

ሀ. ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያንን መመሪያና ሥነ ሥርዓት ጠብቀውና አክብረው መስለፍ ያለባቸው መኾኑን፣

ለ. ስለ መጨረሻው ዘመን ክፋት፣

ሐ. የቅዱስ ጳውሎስ የማስተማር ዘመኑ እያለቀ ስለመሔዱ የሚገልጡ ናቸው::

ይህ መልዕክት አራት ምዕራፍ አለው::

**12. ወደ ቲቶ የተላከ:-**

ይህም ከግብረ ኖሎት መልዕክታት ሦስተኛው ነው::

ቲቶ በአንጾኪያ የተወለደ አረማዊ ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ አጥምቆ አስከትሎታል:: በዚህም ምክንያት እንደ ጢሞቴዎስ ለቅዱስ ጳውሎስ እውነተኛና ታማኝ ልጅ ነው::/ቲቶ1÷4::/ እየተላከ ብዙ መልዕክታትን በየቦታው አዳርሷል:: በመጨረሻም በቀርጤስ /ክሬት:- ክሪቲ በታላቁ ባህር በስተ ደቡብ የምትገኝ የግሪክ ደሴት ናት / የመጀመሪያው ጳጳስ አድርጎ ሾሞታል:: /ቲቶ 1÷5::/ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያው የቀርጤስ ጳጳስ ቲቶ ነው:: /EUS. HE lll. Iv.b /

በዚህ መልዕክት ውስጥ ካሉት ዋና ዋና ነጥቦች ውስጥ:-

ሀ. የቲቶ ሹመት በቀርጤስ

ለ. ስለ ካህናት ሹመት መለኪያ፣

ሐ. አሮጊት እናቶች ወጣቶችም ቢኾኑ በቤተ ክርስቲያን የሥራ ድርሻቸውን እንዲያውቁ ምክርና መመሪያ፣

መ. ቲቶ ሳይፈራ እንዲያስተምር ለቲቶ ለራሱ መመሪያ

ሠ. እሱ ዘንድ ያሉት ሰዎች ያቀረቡትን ሰላምታ ለቲቶ ይነግረዋል::

ይህ መጽሐፍ ሦስት ምዕራፍ አለው::

**13. ወደ ፊልሞና የተላከ መልዕክት:-**

ፊልሞና የቆላስዮስ ሰው ነው:: ያጠመቀው ቅዱስ ጳውሎስ ነው:: ይህ ሰው ባለጸጋ ነው:: ሐዋርያትንም እየተቀበለ ያስተናግድ ነበር:: ቅዱስ ጳውሎስ በሮም በእስር ቤት ሳለ የፊልሞና አገልጋይ የሚኾን አናሲሞስ ከጌታው አምልጦ ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ኮበለለ:: ቅዱስ ጳውሎስ አናሲሞስንና ፊልሞናን ለማስታረቅ የጻፈው መልዕክት ነው:: ከአራቱ የእስር ቤት መልዕክታት አራተኛው ይህ ነው:: ከቅዱስ ጳውሎስ መልዕክታት አንድ ምዕራፍ ብቻ ያለው ይህ ብቻ ነው::

በዚህ መልዕክት ውስጥ ካሉት ነጥቦች:-

ሀ. ሰላምታ፣

ለ. አናሲሞስን እንዲቀበለው፣

ሐ.በክርስትና ወንድማማችነት እንጅ የባሪያና ጌታ ሥርዓት የሌለ መኾኑን ለፊልሞና ገልጦለታል::

ይህ መጽሐፍ አንድ ምዕራፍ ብቻ አለው::

**14. ወደ ዕብራውያን የተላከ:-**

መጽሐፍ ቅዱስ እስራኤልን /ከመከፋፈላቸው በፊት / በኹለት ይጠራቸዋል፤ አንዱ ዕብራውያን የሚል ነው። ለዚህም ኹለት ምክንያት አለው። አንዱ በአያታቸው በሴም የልጅ ልጅ በዔቦር ነው። ዔቦር የነገድ አባት ኹኖ በሱ ተጠርተዋል። /ዘኁልቁ 24÷ 24፡፡/ ኹለተኛው ምክንያት ከአብርሃም ፍልሰት ጋር የተያያዘ ነው፤ አብርሃም ኤፍራጥስንና ጤግሮስን ተሻግሮ ተጉዞ ወደ ከነዓን ምድር ሲገባ የከነዓን ሰዎች ዕብራዊ መጣ ብለውታል፡፡/ዘፍጥ14÷13፡፡/ ወንዝ ተሻግሮ የመጣ ማለት ነው።

«ዕብር»ማለት «መሻገር» ማለት ነውና። ቋንቋቸውም «ዒብሪት» «ዕብራይስጥ» ይባላል/የሐዋ. ሥራ 21÷ 40፡፡22÷20፡፡/ ቅዱስ ጳውሎስ ራሱን ዕብራዊ ነኝ ብሎ ይጠራ ነበር፡፡/ካል. ቆሮ. 11÷ 22፡፡ ፊልጵ 3÷5፡፡/

ኹለተኛው ስማቸው «እሥራኤል» ነው። ይህ ስም ከያዕቆብ ያገኙት ነው። ያዕቆብ በሕልሙ እግዚአብሔር ተገለጠለት ካልባረከኝ አልለቅቅህም ብሎ ቀሚሱን ጨምዶ ያዘው። እግዚአብሔርም ባረከው። አዲስም ስም ሰጠው። «እስራኤል» አለው። /ዘፍጥ.32÷ 22-32/ እስራኤል ማለት «ከእግዚአብሔርም ከሰውም ጋር ይታገላል ያሸንፍማል ማለት ነው»። /ዘፍጥ. 35፣ 9-11፡፡/ ቅዱስ ጳውሎስ ይህን መልዕክት የጻፈው ለክርስቲያን ዕብራውያን ነው። በዚህ መልዕክት ውስጥ የተጠቀሱ ነጥቦች:-

ሀ. የእግዚአብሔር መግቦት ከሰው ሳይለይ መኖሩ፣

ለ. ለመጨረሻም በልጁ ሞት ዓለምን ማዳኑ፣

ሐ. የእግዚአብሔር ልጅ አምላክ እንጅ መልአክ አለመኾኑ፣

መ. የእግዚአብሔር ልጅ ሙሴን የላከ እንጅ እንደ ሙሴ ነቢይ አለመኾኑ፣

ሠ. የመልከ ጼዴቁ ክህነት ለቤተ ክርስቲያን ክህነት አወራረስ ምሳሌነቱ፣

ረ. ከብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ መብለጡ በዝርዝር ተገልጧል።

ይህ መልዕክት አሥራ ሦስት ምዕራፍ አለው።

***ከጳውሎስ መልዕክታት በኋላ ሰባት የሐዋርያት መልዕክታት አሉ።***

**1. የጴጥሮስ መልዕክት ቀዳማዊ:-** /በአትናቴዎስ የአቆጣጠር ተራ ከጳውሎስ መልእክታት ቀጥሎ የያዕቆብን መልዕክት አስቀምጧል /

ጴጥሮስ ሦስት ስሞች አሉት። ስምዖን፣ ኬፋ፣ ጴጥሮስ። ስምዓንና ኬፋ የአራማይክ ስሙ ነው። ጴጥሮስ የግሪክ ስሙ ነው። በአራማይክ ኬፋ በጽርዕ/ግሪክ/ ጴጥሮስ ደንጊያ ማለት ነው። ጴጥሮስ ትውልዱ በገሊላ ቤተ ሳይዳ ነው። /ዮሐ. 1÷45፡፡/ ዓሣ በማጥመድ ላይ እንዳለ ከገሊላ ሐይቅ ዳር ለሐዋርያነት ተጠራ/ማቴ. 4÷18፡፡/ በሦስት ዓመት ከሦስት ወር የትምህርት ጊዜው ጴጥሮስ እንደ ጓደኞቹ ሐዋርያት ጌታን በእጁ ዳሰታል ቃሉን ሰምቷል በዓይኑ አይቶታል እንዲያውም ከሌሎች ወንድሞቹ በዕድሜ ብልጫ ስላለው/ቀዳ. ጴጥ. 1÷1፡፡/ ከጌታ ጋር መላልሶ ይናገር ነበር።

አንዳንድ ጊዜም ጌታ ይገሥፀው ነበር። በማቴዎስ 16 ፥ 16 ጌታ ለሐዋርያት ላቀረበው ጥያቄ ጴጥሮስ በሐዋርያት ስም ተገቢውን መልስ ሰጥቶ መልሱ ተመስግኗል። በዚሁ ምዕራፍ ላይ በቁጥር 23 አነጋገሩ ከጌታ ዕቅድ ጋር ሳይስማማ ቀርቶ ተገሥጿል።

ጴጥሮስ በልቡ ቅንነት ኹሉን ለማድረግ የሚችል የሚመስለው የእግዚአብሔርን ምስጢር ግን የማያስተውል ባለማስተዋሉም የሚወድቅ እግዚአብሔር ግን የልቡን ቅንነት አይቶ እንደገና የሚያዝንለት የዋህ ሰውን ይመስላል። ለዚህም ጌታ ምሥጢረ ሕማማቱን ለሐዋርያት በነገራቸው ጊዜ ጴጥሮስ በየዋህነት የመለሰውን መልስ በዚህም ምክንያት በጴጥሮስ ላይ የደረሰበትን አደጋ ማየት በቂ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክም ኾነ በመጽሐፍ ቅዱስ የክርስቲያኖች ማዕከል ኢየሩሳሌም ናት፣ የጴጥሮስ የመጀመሪያ መንበርም አንጾኪያ ናት። በመጨረሻም ወደ ሮም ሔዶ በ64 ዓ.ም በኔሮን ቄሳር ዘመነ መንግሥት ቁልቁል በሰማዕትነት ሙቷል፣ ይህም በኢትዮጵያ አቆጣጠር ሐምሌ አምስት ቀን ነው፡፡/ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር መኾኑ ነው፡፡/

ጴጥሮስ በሮም ከተማ በመገደሉና በማቴዎስ 16፣18 በሉቃስ 22፣ 31-32። በዮሐንስ 21፣15-17። የተነገረውን ኹሉ በማጠራቀም የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጴጥሮስ የሞተባት ሮምን የክርስቲያኖች ማዕከል ጴጥሮስን የቤተ ክርስቲያን አለቃ የሮማ ፓፓዎችም የጴጥሮስ ወራሾች የማይሳሳቱ የቤተ ክርስቲያን ምስክሮች እንደኾኑ በማስተማር ለብዙ አመታት ቆይታለች።

በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ትውፊቱንና ኦርቶዶክሳዊ ትምህርቱን ያላፋለሰ ከኾነ ማንኛ ውም ኤጲስ ቆጶስ የአሥራ ኹለቱም ሐዋርያት ወራሽ ነው ። ስለዚህ ነው ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያት ጉባኤ ናት የምንለው። እነሱ እንደሚሉትማ ከኾነ እያንዳንዱ ሐዋርያ በሞተበት ቦታ የተለየ ምስክርነት አለው ያሰኛል። በማዕከልነትም ቢኾን ክርስቶስ የተወለደባት፣ ያደገባት፣ ያስተማረባት በመስቀል ተሰቅሎ የሞተባት ኢየሩሳሌም እያለች ሮም/ቫቲካን/ የክርስቲያኖች ማዕከል ናት ማለት እግዚአብሔርን ማሳዘን ነው። በመንበርነትም ቢኾን ከሮም በፊት የጴጥሮስ መንበር አንጾኪያ ነበረች። እንግዲያውስ በሥጋዊ አገዛዝ የነበረውን የቄሳር መንፈስ በቤተ ክርስቲያን ለማሳደግ ካልኾነ በቀር ለክርስትና ማዕከል አኹንም ኢየሩሳሌም ናት።

ጴጥሮስ ከሐዋርያት መካከል በዕድሜ የበላይነት ስላለው/ቀዱ. ጴጥ. 5፣1.1።/ ለትምህርት ቤቱ እንደ አለቃ ለጓደኞቹም እንደ ታላቅ ወንድም ያለ የአክብሮት የበላይነት ነበረው ከላይ የጠቀስናቸው የጌታ ንግግሮችም ይህን የሚመለከቱ ናቸው። ነገር ግን የጌታን ቃል ጠልፎ በሮማዊ ልማድ የገዥነትን መረብ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተጣለውን ሰው ሰራሽ የቀኖና መረብ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን አትቀበለውም። ይህን ማለትም የጴጥሮስን ቅዱስነት አይቀንሰውም።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጴጥሮስ ኹለት መጽሐፎች አሉት። በመጀመሪያው መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ነጥቦች:-

1. ክርስቲያኖች በተጠንቀቅ እንዲኖሩ፣ በሕይወታቸው ቅድስና እንዲታይባቸው።
2. ክፋትንና በቀልን እንደማያስቡ ሕጻናት እንዲኾኑ፣
3. የእግዚአብሔር ቤት እንዲኾኑ፣
4. ለባለ ሥልጣኖች እንዲታዘዙ፣
5. ገዢና ተገዢ፣ ወላጆችና ልጆች፣ ባልና ሚስት እንዲዋደዱና እንዲከባበሩ፣
6. በመከራ እንዲበረቱ፣ በመጠን እንዲኖሩ፣ በትሕትና ኹነው የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዲጠብቁ፣
7. ጠላት ሰይጣን እንዳይውጣቸው እንዳይዘናጉ ለምዕመናን ኹሉ አደራ ብሏል። ይህ መልዕክት አምስት ምዕራፍ አለው።

<u>2. ኹለተኛይቱ የጴጥሮስ መልእክት:-</u>

1. ስለራሱ መጠራት/ሞት/
2. ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መሰረታዊ የት መጣ፣
3. ሐሰተኞች ነቢያትና ድፍረታቸው፣
4. የአለም ፍጻሜና የክርስቲያኖች ተስፋ በዚህ መልዕክት ውስጥ ዋናውን ቦታ ይዟል። ይህ መልዕክት ሦስት ምዕራፍ አለው።

<u>3. የዮሐንስ መልዕክት ቀዳማዊ:-</u>

ዮሐንስ ወንጌልን የጻፈው /ታሪኩን በወንጌሉ መግለጫ ላይ እዩ/ ሦስት መልዕክታት አሉት።

*መልዕክተ ቀዳማዊ:-*

1. የሐዋርያት ምስክርነት ትክክል መኾኑን፣
2. ከጥምቀት በኋላ ኃጢአት መስራት የማይገባ መኾኑን፣
3. የሐሣዊ መሲህን መምጣት፣
4. የእግዚአብሔር ልጅ ሰው መኾኑን/ሥጋ መልበሱን/ የማያምን ኹሉ ሐሳዊ መሲሕ መኾኑን፣
5. ወልድን ካላመኑ አብን ማመን የማይቻል መኾኑን፣
6. እምነትና ምግባር የተዋሐዱ መኾናቸውን ይህ መልዕክት ያስተምራል። ይህ መልዕክት አምስት ምዕራፍ አለው።

<u>4. ኹለተኛይቱ የዮሐንስ መልዕክት:-</u>

ይህ መልዕክት:- አንድ ምዕራፍ ብቻ ነው። በውስጡም:-

1. የክርስቶስን ሥጋዌ የሚያስተባብሉ መናፍቃን መነሳታቸውን በመግለጥ ምዕመናንን የሚያስጠነቅቅ፣
2. ከመናፍቃን ጋር ጓደኛ መኾን የማይገባ መኾኑን የሚመክር መልዕክት አለበት::

**5. ሦስተኛይቱ የዮሐንስ መልዕክት:-**

ይህም መልክት አንድ ምዕራፍ ብቻ ነው:- ይህ መልዕክት የያዘው

1. በስደት ጊዜ ክርስቲያኖችን የተቀበለውን ሰው ስምና የቀረበለት ሰላምታ
2. በሃይማኖት ምክንያት የተሰደዱትን ክርስቲያኖች ተቀብሎ ማስተናገድ ክርስቲያን ለኾኑ ኹሉ የሚገባ መኾኑን ነው::

**6. የያዕቆብ መልዕክት**

ይህ ያዕቆብ የዮሴፍ ልጅ ነው:: ከጌታ ጋር አብሮ ስላደገ «የጌታ ወንድም» የሚል ቅጥል አለው እሱ ግን ራሱን የሚጠራው «የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ያዕቆብ» እያለ ነው:: በሐዋርያነት አገልግሏል::

ያዕቆብ በኢየሩሳሌም የመጀመሪያው ጳጳስ ነበር የተሾመውም በጌታና በሐዋርያት ነበር::/EUS. EH VII.19/ በ50 ዓ.ም የተደረገውን የሐዋርያት ጉባኤ በሊቀመንበርነት የመራውና ውሳኔውንም በአሕዛብ አገር /አንጾኪያ፣ ሶርያና ቂልቅያ / ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ኹሉ እንዲተላለፍ ያደረገው ይኸው ያዕቆብ ነው:: /የሐ.ሥ 15÷19-23::/ ቅዱስ ጳውሎስ ለመጨረሻ ጊዜ ኢየሩሳሌምን ሲጎበኝ ባደረገለት ጥያቄ ያዕቆብ ከአይሁድ ለተመለሱትም ክርስቲያኖች የሚያስብላቸው መኾኑን ያሳያል:: /የሐ.ሥራ 21÷18::/ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን እንደሚለው ይህ ያዕቆብ በኢየሩሳሌም ሰዎች ዘንድ «ጻድቁ ያዕቆብ» እየተባለ ይጠራ ነበር:: ያባቶቹን ሕግ አክባሪ በጾምና በትሕርምት ኗሪ ስለነበር /EUS.EH ii.23/ በኢየሩሳሌም የክርስቲያኖችን አንድነት ጠብቆ በሰላም በመምራት ላይ እንዳለ በአይሁድ ሊቀ ካህናት በሐናንያ አነሳሽነት በደንጊያ ተወግሮ በሰማዕትነት ተገደለ:: ይኸውም የኢየሩሳሌም ገዢ የነበረው ፌስጦስ ከሞተ በኋላ ነው:: /JOS Ant. Xx.9./ ከያዕቆብ ጀምሮ በተከታታይ በኢየሩሳሌም የተሾሙት አሥራ አምስት ኤጲስ ቆጶሳት ከቤተ አይሁድ የተመለሱ እሥራኤላውያን ናቸው:: /Father Yacoub KORIAH "KARKENNY" The Synion ORTHODOX CHURCH in the Holy Land, Jeruralem,1976/ ይህ ያዕቆብ አምስት ምዕራፍ የያዘ መልዕክት በሐዲስ ኪዳን ውስጥ አለው:: በመልዕክቱ ከተጠቀሱት ዋናዎቹ::

1. የክርስቲያኖች ትዕግሥትና ትሕትና፣
2. የክርስቲያኖች መከባበርና እኩልነት በሥርዓተ ማኅበራቸው አድልዎ እንዳይታይ፣
3. የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ብቻ ሳይኾን በሥራ ማሳየት፣
4. ምግባር የሌለው እምነት ነፍስ የተለየው ሥጋ ይመስላል፣
5. ያለ ችሎታ ለማስተማር መሻማት ወደ መናፍቅነት ይጥላል፣
6. ሕግን መጠበቅ ኹሉንም እንጅ በከፊል እየጠበቁ በከፊል አለመጠበቅ ዋጋ የሌለው ነው፣
7. ድሆችን የሚንቁና የሚበዘብዙ ባለጠጎችን ይወቅሳል ድሆችም እንዳይቸኩሉ የኢዮብን ትዕግስት ያስተምራቸዋል፣
8. በጠቅላላ በያዕቆብ መልዕክት ትክክለኛ ሃይማኖት ማለት በጥሩ ሥራ የሚገለጥ እንጂ የቃል ትምህርት አይደለም::

**7. የይሁዳ መልዕክት:-**

ይህ ይሁዳ የያቆብ ወንድም ነው። በማቴዎስ 13 ፥ 55 የጌታ ወንድሞች ተብለው ከተጠሩት የዮሴፍ ልጆች አንዱ ነው:: ይሁዳ ግን «የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ የያዕቆብ መንድም መኾኑን እንጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም ነኝ» አላለም::

ይህ ይኹዳ በሐዋርያነት አገልግሏል:: መልእክቱም አንድ ምዕራፍ ብቻ ነው:: በውስጡም:-

1. ስለ መናፍቃን በቤተ ክርስቲያን ላይ መነሳት፣
2. በእግዚአብሔር ላይ የሚነሱ መናፍቃን በቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይኾኑ በብሉይ ኪዳን ጊዜም በብዛት እንደነበሩ፣
3. ምዕመናን ራሳቸውን ከተሳሳተ ትምህርት ጠብቀው የሚሳሳቱትንም ለማዳን መሞከር እንጅ ዝም ማለት እንደማይገባ ጠቃሚ ትምህርት አለው::

**8. የዮሐንስ ራዕይ፡-**

ይህን ራዕይ ያየውና የጻፈው ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው፡፡ ዮሐንስ በዚሁ ራዕይ ውስጥ እንደገለጠው የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ኹኖ ሲያስተምር በሮማውያን ባለስልጣኖች ተይዞ በቄሳር ድምጥያኖስ ትእዛዝ በደሴተ ፍጥሞ ታሰረ/ራዕይ 1÷9-10/ በዚያም በዋሻ ውስጥ ተዘግቶበት እያለ ይህን ራዕይ አየ፡፡ ይህ ራዕይ በዓለምና በቤተ ክርስቲያን የነበረውን፣ ያለውንና የሚመጣውን የሚያጠቃልል ነው፡፡ በእርግጥ ቃሉና መልዕክቱ ከእግዚአብሔር የመጣ ስለኾነ የሰው አቅም በዘመንና በታሪክ ሊሸነሽነው ባይችልም ባጠቃላይ መልኩ ሲታይ፡-

1. የአብያተ ክርስቲያንን ስደት፣
2. የሐሳዊ መሢህን መምጣት፣
3. የሰማዕታትን መከራና የዓለምን ፍጻሜ፣
4. የእግዚአብሔርን የፍርድ ቀን፣ የመንግሥተ ሰማያትን መምጣት፣
5. የክርስቶስን ዳግም ምጽአትና የሚሰጠውንም ሽልማት፡- ዮሐንስ በዚያች በታሰረባት ዋሻ አይቷል፡፡

ይህ መጽሐፍ ሃያ ሁለት ምዕራፍ የያዘ ነው፡፡

# ክፍል ሦስት

<u>ጥያቄ:-</u> የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ወደ ሀገራችን ቋንቋ የተመለሱበት ጊዜ ይታወቃል ወይ?

<u>መልስ:</u>- ሁሉም ባንድ ዘመን ወይም ባንድ ላይ ተመልሰዋል ለማለት ቢቸግረንም ከጌታ ልደት በፊት አንድ ሺህ ዓመት ቀደም ብሎ ነው፤ ይኸውም የሀገራችን ንግሥት ማክዳ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ወደ ኢየሩሳሌም ከሄደችበት ጊዜ ጀምሮ ነው።

<u>ጥያቄ:</u>- ወደ ግዕዝ ቋንቋ የተመለሰው ከምን ቋንቋ ነው? ይህንንም ያልኩበት ምክንያት አለኝ። በአለፈው ሲያስተምሩኝ ሰባ ሊቃናተ የመለሱት የፅርዕ ብሉይ ኪዳን ሄሮኒሞስ የመለሰው የላቲን ብሉይ ኪዳን ስላለ ነው።

<u>መልስ:</u>- አይ! ለዚህ ሁሉ እኮ ዘመኑ ራሱ ያስታውቅሃል የፅርዑም የላቲኑም የተመለሱት በኋላ ነው። እንዲያውም የላቲኑማ በአዲስ ኪዳን ዘመን ነው። የኛ ግን እንደነገርሁህ ከሁሉም የራቀ ቅድሚያ ስላለው ከዕብራይስጡ ነው። ለዚሁም አባቶች የመዘገቡትን ከዚህ በታች ተመልከት።

«ወመክብበ መጻሐፍቲሃሰ ዘብሉይ ተዕልዋ እምእብራይስጢ ኀበ ግዕዝ በመዋዕሊሃ ለንግሥተ አዜብ እንተ ሐወጸቶ ለሰሎሞን ወበእንተዝ ኮነ ጽሩየ የፍንሬሆሙ ለመጽሐፍተ ነቢያት ዘወስተ ብሔረ እግዓዚ እስመ በሕገ አይሁድ ነበሩ እምቅድመ ልደቶ ክርስቶስ ወእመስኬ አለውዎ እምድኅረ ልደተ ክርስቶስ ሜጡ ሰቃልያን ቃለ ጽድቀ ውስተ ስምዐ ሐሰት ወከመሰ ተዐልዋ መጽሐፍተ ነቢያት እምእብራይስጢ ኀበ ግእዝ ትረክብ ትእምርተ በውስተ መጽሐፈ ነገሥት ዘይብል ትርጓሜ ነገረ ዕብራይስጢ ኀበ ግእዝ ኤሎሄ ብሂል አምላክ አዶናይ ብሂል እግዚእ ጸባኦት ብሂል ዘኀይላት።»

ከዚህ በላይ እንዳየኸው ያባቶቻችን መዝገብ እንዳቆዩን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ወደ ግዕዝ የተመለሱት ከእብራይስጥ ነው። አንዳንድ ሰዎች ግን ይህን በመቃወም ብሉይ ኪዳናችን ውስጥ አልፎ አልፎ የሚታዩ የፅርዕ ነክ ስሞችን ይዘው የኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳን የተመለሰው ከሰባ ሊቃናት ፅርዕ ነው ይላሉ። ይህ አመለካከት የእምነታችንንም የታሪካችንንም አቋም ስለሚጎዳው በጥንቃቄ መመልከት ያስፈልጋል።

<u>ጥያቄ</u>:- የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትስ መቼ ተመለሱ?

<u>መልስ</u>:- የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ወደ አገራችን ቋንቋ ወደ ግዕዝ የተመለሱት ከመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ ፍሬምናጦስ/አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን/ ጀምሮ ነው። አዲስ ኪዳን ወደ ሃገራችን የተመለሰው ከፅርዕ ቋንቋ ነው።

<u>**ጥያቄ**</u>:- የግዕዝ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው በስንት ዓመተ ምህረት ነው?

<u>**መልስ**</u>:- ለመጀመሪያ ጊዜ በኅትመት የዋለው የዳዊት መዝሙር ነው። ይህ ኅትመት የተካሄደው በ**1514** ዓ.ም ነው። ይህ የኅትመት ሥራ ሊሳካ የቻለው አባ ጎርጎርዮስ/ዘመካነ ሥላሴ ወረኢሉ/ በሚባሉ ኢትዮጵያዊ መነኩሴ ነው። እሳቸው ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው በዚያው የጴጥሮስንና የጳውሎስን መቃብር ለመሳለም ወደ ሮም ተጓዙ እዚያው እንዳሉ ዮሐንስ ፖትከን ለሚባል ሰው የግዕዝ ቋንቋ አስተማረ። ከዚህ በኋላ ኹለቱ ተባብረው የዳዊት መዝሙር ለመጀመሪያ ጊዜ በሮም ታተመ።

<u>**ጥያቄ**</u>:- የአዲስ ኪዳን መጽሐፍስ በግዕዝ ቋንቋ በየት አገር በስንት ዓመተ ምህረት በኅትመት ዋለ?

<u>**መልስ**</u>:- የአዲስ ኪዳን በግዕዝ ቋንቋ ለመጀመሪያ የታተመው በ**1548** ዓ.ም በሮም ነው። ይህ አዲስ ኪዳን የተገኘው አባ ተስፋ ጽዮን ከሚባሉት መነኩሴ ነው። አባ ተስፋ ጽዮን ከኢትዮጵያ ታላቅ ገዳም ከደብረ ሊባኖስ ነው። ከላይ እንደሰማኸው ብዙ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን መነኮሳት ኢየሩሳሌምን ለመሳለም በእግራቸው ይጓዛሉ። ብዙዎቹ አውሬ እየበላቸው ይቀራሉ። ሌሎቹ ደግሞ በውሃ ጥም ያልቃሉ። ጥቂቶች በጭንቅ ይደርሳሉ ከደረሱ በኋላም የጴጥሮስንና የጳውሎስን መቃብር ለመሳለም በረከት ለመቀበል ወደ ሮማ ይሔዱ ነበር። ከዚያም የተነሳ ከኢትዮጵያዊ ቋንቋቸውና በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነታቸው የሚገለገሉበት በቫቲካን የጸሎት ቦታ ተፈቅዶላቸው በስማቸው የሚጠራ የእስጢፋኖስ ገዳም ነበራቸው ይህም ለብዙ ዘመናት ከኦርቶዶክሳውያን እጅ ከቆየ በኋላ ዛሬ ግን መልካቸውና ትውልዳቸው ኢትዮጵያዊ ይኹን እንጅ በእምነት የሮማ ካቶሊክ ዜጎች የኾኑ መነኮሳት ይገለገሉበታል።

<u>**ጥያቄ**</u>:- መጽሐፍ ቅዱስ ወደ አማርኛ ቋንቋ እንዴት እንደተመለሰና መቼ እንደተመለሰ ቢነግሩኝ በጣም ደስ ይለኛል ነበር።

<u>**መልስ**</u>:- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ ቋንቋ በሐተታና በአንድምታ /አስተያየትና አወራረድ/ የተተረጎመው በአሥራ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው። ይኸውም አማርኛ በግዕዝ ቦታ ተተክቶ የሀገሪቱ ብሔራዊ ቋንቋ ከኾነበት ጊዜ አንስቶ ነው። ፈረንጆች ግን በነጠላ ትርጓሜ ካይሮ ላይ በፈረንጆች አቆጣጠር ከ**1808-1818** ዓ.ም ከዐረብኛው ዘር የተተረጎመውን ብቻ

ነው የሚያውቁት፡፡ ይህን የነጠላ ትርጓሜ ያዘጋጁት ሰዎች በካይሮ ይኖሩ የነበሩ «አቡ ሩሚ»/ይህ ስም ኢትዮጵያዊ አይደለም አቡ ሩሚ ያሏቸው ዐረቦች ናቸው፡፡ ሰውዬው ከፈረንጆች ጋር ስለሚታዩ ዐረቦች የሮማውያን ወዳጅ እንደማለት አቡ ሩሚ ብለዋቸው ይኾናል / የሚባሉ ከጎንደር የሔዱ ኢትዮጵያዊና አሴላንዲ/"M. Asselin Cherville"/ የተባሉ በካይሮ የፈረንሳይ ቆንስል ናቸው፡፡ ይህ አሥር ዓመት የፈጀ ድካም ባይናቅም ለአማርኛ ትርጓሜ ግን የመጀመሪያው ነው አንለውም፡፡

በዚሁ ከአቡ ሩሚ ነጠላ የመጽሐፍ ቅዱስ የአማርኛ ትርጓሜ በፈረንጆች አቆጣጠር 1824 ዓ.ም አራቱ ወንጌሎች በለንደን ታተሙ፡፡ /Evangelia Sancta, Sub auspcìis D.Asselini, rerum gallicarum apud Aegyplios procuratoris, in linguam, vertic Abu Rumi Habissimus, edit th. Pell platt,London.1824/ ደግሞ እንደገና በዚሁ በለንደን ከተማ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1824 ዓ.ም በከአቡሩሚ ትርጓሜ ላይ ሙሉው ሐዲስ ኪዳን ታተመ፡፡/Testamentum Novum Domini Nostri ed th. P. platt London 1829/

በመጨረሻም ሙሉው የአቡሩሚ የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ በፈረንጆች አቆጣጠር በ1840 ዓ.ም በለንደን ታተመ፡፡/Bibila sancta Amharica sub auspiciis D Assellini ed. T.P. platt, London, 1840/

የመጀመሪያው ቅዱሳት መጻሕፍት በአማርኛ ቋንቋ የማተሙ ኹኔታ በዚህ ዓይነት ነበር፡፡ አኹንም ቢኾን ሚሲዮናውያን የመጻሕፍትን ቃል ለሃሳባቸው እንደሚመች እያደረጉ በመለዋወጥ በብዙ የሃገራችን ቋንቋዎች ቅዱሳት መጻሕፍት እያሉ በመሉም ኾነ በከፊል በማሳተም ላይ ናቸው፡፡

በሀገራችን ርእሰ ከተማ በአዲስ አበባ ቤተ ማኅተም ከተቋቋመ አንስቶ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት በግዕዝና በአማርኛ እየኾኑ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ ታትመዋል፡፡

**ለምሳሌ፡-**

- ❖ የዮሐንስ አፈወርቅ መጽሐፍ /ተግሳጽ/ንባብና ትርጓሜ በ1914 ዓ.ም
- ❖ የአርባዕቱ ወንጌል ንበብና ትርጓሜ በ1915 ዓ.ም
- ❖ የማር ይስሐቅ መጽሐፍ ንባብና ትርጓሜ በ1915 ዓ.ም
- ❖ የሰሎሞን መጽሐፍትና ሲራክ ንባብና ትርጓሜ በ1916 ዓ.ም
- ❖ የሕዝቅኤል መጽሐፍት ንባብና ትርጓሜ በ1916 ዓ.ም
- ❖ የትምህርተ ኅቡዐትና ኪዳን ንባብና ትርጓሜ በ1916 ዓ.ም
- ❖ የውዳሴ ማርያምና የቅዳሴ ማርያም ንባብና ትርጓሜ በ1917 ዓ.ም
- ❖ የአሥራ አራቱ ቅዳሴያት ንባብና ትርጓሜ በ1918 ዓ.ም
- ❖ አርባዕቱ ወንጌልና ግብረ ሐዋርያት በነጠላ ትርጓሜ በ1922 ዓ.ም
- ❖ ፊልክስዩስ ንባብ ከነ ትርጓሜ በ1920 ዓ.ም
- ❖ አረጋዊ መንፈሳዊ ንባብ ከነ ትርጓሜ በ1922 ዓ.ም
- ❖ የዮሐንስ አፈወርቅ ድርሳን ንባብ ከነትርጓሜ በ1923 ዓ.ም

በእነዚህ መጽሐፎች ለብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት ማሚሻ ኾነው የታተሙ ሲኾኑ እስካኹንም በቤተ ክርስቲያኒቱ ማተሚያ ቤት «ትንሳኤ ዘጉባኤ» ማተሚያ ቤት አያሌ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ታትመዋል፡፡ በመታተምም ላይ ናቸው፡፡

<u>ጥያቄ</u>፡- አኹን ቤተ ክርስቲያናችን ለወጣቱ ትውልድ የሚጠቅሙ መጽሐፍትን በማሳተም ላይ እንደኾነች ቢነግሩኝ?

<u>መልስ</u>፡- አዎ ጥራቱን እየመረመረች በርካታ መጻሕፍትን ታትማለች፡፡ የመጻሕፍት ብዛታቸው ብቻ ሳይሆን የሚጠቅመው ጥራታቸውም ነው፡፡ ለወደፊቱ ጥራታቸው እየተመረመረ የተዋሕዶ ሃይማኖታችንን ትውፊት ለትውልድ ለማስተላለፍ የሚበቁ መጻሕፍት ቢታተሙ ወጣቱ ትውልድ ከስህተት ይጠቃል፣ ቤተ ክርስቲያናችንም አትወቀስም ብዙ ጸሐፊዎች ብዙ ዝግጅት ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ ለተዋሕዶ ሃይማኖታችን የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን የማጣራት መብት ግን የቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ምን ጊዜም ቢኾን አውቃለኹ የሚል አይጠፋም ኹሉም ልጻፍ ላስተምር ይላል ታዲያ ትምህርቱ የሚፈለገውን ለቆ የማይፈለገውን የሚያቀብል እንዳይሆን ወይም የሚፈለገውን ከማይፈለገው ጋር የሚቀላቅል እንዳይኾን በስሟ ስለሚታተሙ መጻሕፍት ቤተ ክርስቲያናችን ጥንቃቄ ማድረግ ተግባሯ ነው፡፡ ለኹሉም ነገር ቢኾን ከመንፈሳዊነት ጋር ጸሎት ያስፈልጋል፡፡

ለምዕመናን በመጠኑም ቢኾን የተዘጋጀው መመሪያና ማስተማሪያ ይህ ነው፡፡ ነገር ግን በመግቢያው ላይ እንደተገለጠው ይህ ዝግጅት አስታዋሽና አንቂ ስለኾነ ሌሎችን የቤተክርስቲያን መጻሕፍትንና የመምህራን ትምህርታቸውን በማንበብና በመከታተል እንድታሰፉት አደራ እንላለን፡፡

**ይቆየን፡፡**